# ታቦት ከአይሁድ ባሕል ወደ ክርስትና

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለጥርጠር የአይሁድ ባህል ከሆኑት ሥርዓቶች መካከል አብዛኞዎቹ በአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጠቃለው እስካሁን ድረስ በሥራ ላይ ናቸው ። እነርሱም ፣ ግዝረት ፣ የምግብ ሥርዓት ፣ የሰንበት ጉዳይ (የቀዳሚት ሰንበት) ፣ ናቸው ። ለዚህ ሁኔታ ምክንያት የሚሰጠው ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የአይሁድ ባህል ትከተል ስለነበርና እንደ ክብረ ነገሥት አገላለጽ የአይሁድን የአምልኮ እና የመስዋዕት ሥርዓት ተቀብላ ስለነበር ክርስትና ከገባ በኋላ እነዚህን ሥርዓቶች ከክርስትና ትምህርት ጋር እያያዘች መጠቀመዋን ቀጥላለች የሚል ነው ። ይህ በእንደዚህ ሁኔታ በግልጽ ተቀምጦ ሳለ ፣ በሌላ በኩል ጉዳዩን በቅርብ ስንመረምር ፥ በቀድሞ የሃይማኖት አባቶች እና ነገሥታት ይሠራባቸው ከነበሩት እንደዚሁም በፍተሐ ነገሥት ላይ ከሠፈሩት መመሪያዎች ጋር ግጭት እንደሚፈጥር ተመልክተናል ። በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አቋም የለም ። በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ዘንድ በውስጥ ታዋቂነት የሚታወቅ ነገር ሆኖ ሳለ ምዕመኑ ግን እስካሁን ድረስ በጥብቅ እነዚህን ሥርዓቶች መፈጸም እንዳለበት ያምናል ።

እንደገናም ኢትዮጵያ ክርስትናን ከተቀበለች ወዲህ "ከሌሎች ክርስቲያን አገሮች በተለየ ሁኔታ የብሉይ ኪዳን ሥርዓትና ሕግን ወደ ክርስትና ሕግና ሥርዓት ለውጣ" እንደምትጠቀምበት ተመልክተናል ። ከነዚህ ሕግና ሥርዓቶች መካከል ዋነኛውና ማዕከላዊው የታቦት ሥርዓት ነው ። የታቦቱን ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥ በተመለከተ ባደርግነው ንባብ በአመጣጡ ላይ ሁለት ዓይነት እምነት እንዳለ ፣ (ወደ ኢትዮጵያ አልመጣም የሚሉትን አመለካከቶች ሳይጨምር) ፣ በነዚህም አመለካከቶች መሠረት ታቦቱ በንግሥት ሳባና በልጇ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከእሥራኤል ቤተ መቅደስ ተሰርቆ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ በዚያም በአክሱም እንደተቀመጠ ፣ ሌላኛው አመለካከት ደግሞ ከንጉሥ ሰለሞን ዘመነ መንግሥት በኋላ ቆይቶ በንጉሥ ምናሴ ዘመነ መንግሥት አይሁዶቹ ከንጉሡ አስከፊ አመራር ለመሸሽና ታቦቱን ለመጠበቅ አስበው በግዞት ወደ ግብጽ ይዘውት እንደሄዱ በዚያም ቤተ መቅደስ ሠርተውለት እንደነበር ፣ ከዚያም ቤተ መቅደሳቸው ስለፈረሰባቸው ወደ ኢትዮጵያ አምጥተውት

እዚያም በጣና ሐይቅ ለብዙ ዘመን እንደቆየ ፣ ክርስትናም ወደ ኢትዮጵያ በገባ ጊዜ ወደ አክሱም በንጉሥ ኤዛና እንደተወሰደ የሚለው እንደሆነ ተመልክተናል ። የሆኖ ሆኖ ሁለቱም አመለካከቶች ታቦቱ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ይገኛል ብለው እንደሚያመለክቱ ለመገንዘብ ያስችላል ።

ይህንን ምርምር ባደረግንበት ወቅት ግን አንድ በጣም አወዛጋቢ ጉዳይ ማግኘታችን ይህም በሁለተኛ ቀኖና መጽሐፎች በተለይም በመቃቢያን መጽሐፍ የተለየ ቅጂ እንዳለ ይህም ደግሞ ስለታቦቱ የሚናገር ክፍል እንደሆነና በግዕዙና በእንግሊዘኛው ቅጂዎች ላይ ታቦቱ በንጉሥ ናቡከደነጾር ዘመነ መንግሥት በነበረው ወረራ ወቅት ነቢዩ ኤርሚያስ በተራራው ላይ ወስዶ እንደደበቀው በመጨረሻውም ዘመን እግዚአብሔር ምህረቱን በሕዝቡ ላይ ሲያፈስ ሥፍራውን እንደሚገልጸው እንደሚያመለክቱ ተመልክተናል ። ይህ ምንባብ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከሆነና እውነትም የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ በክብረ ነገሥት ላይ ካለው ታሪክ ጋር ሊጣጣም ባለመቻሉ ታሪኩን እንዳለ የሚያፈርሰው እንደሆነ ተረድተናል ።

በአሪት እና በአዲስ ኪዳን ባለው ታቦተ ሥርዓት መካከል ልዩነቶች እንዳሉ እና ለነዚህም ልዩነቶች አጥጋቢና አርኪ መልስ ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ እንዳገኘነውም ተመልክተናል ። ሥርዓተ ታቦት (ከሙሴ ሕግ/ከእሥራኤላውያን ጋር በተያያዘ) ከአይሁድ የአምልኮ ሥርዓት ወደ ክርስትና ይዘት ተመልሶ በጥቅም ላይ ያለው በኢትዮጵያ በኦርቶደክስ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ብቻ ነው ። በማንኛውም ሌላ ቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክስም ይሁን ካቶሊክ ወይም ደግሞ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን ውስጥ ይህ ሥርዓት የለም ። ታቦቱ ያስፈልጋል ከሚባልበት ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ሥርዓተ ቁርባን ለማስፈጸሚያ ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት እንደሆነ የታቦቱን ሥርዓት በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት እንደሆነ በመረመርንበት ጊዜ ተመልክተናል ። በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችም ዘንድ ያለ ታቦቱ ሥርዓተ ቁርባን ሊፈጸም አይችልም የሚል አመለካከት አለ ምክንያቱም ኅብስቱ ወደ ክርስቶስ ሥጋ ወይኑም ወደ ክርስቶስ ደም የሚለወጠው በታቦቱ ላይ በሚፈጸመው ሥርዓተ ጸሎት አማካኝነት ስለሆነ ነው ። ይህንን አስመልክቶ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ጌታ የሆኑት ታቦቱን በተመለከተ "አስፈላጊነቱ የግድ ነው" ብለዋል። ይህ እንደዚህ ከሆነ ሥርዓት ታቦት የሌላቸው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ትክክለኛ የሆነ የቁርባን ሥርዓት አይፈጽሙም ልንል ነው ? ነገር ግን ይህንን ሁኔታ

ለማብራራት የቀድሞ አባ ጎርጎሪየስ ሲጽፉ "ከኢትዮጵያም ሌላ በምሥራቅ ክርስቲያናት (Oriental Churches) ታቦት የተለመደ ሕግ ነው ። ሥጋ ወደሙን የሚፈትቱት በታቦቱ ላይ ነው ። ለምሳሌ ግብጻውያን ታቦቱን "ሉሕ" ይሉታል ጽላት ሠሌዳ ነው ። ያለሱ ሥጋውና ደሙን አይፈትቱም። የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተብለው የሚጠሩ የግሪክ የሩሲያ የሩማኒያ ሌሎችም ወደ ክርስትና የተመለሱት ከአረማዊነት ስለሆነ የታቦትን ምሥጢር አያውቁትም በታቦቱ ፈንታ ከመንበር የማይነሳ እንደ ታቦት የሚከበር የጌታ የስቅለቱ ወይም የግንዘቱ ሥዕል ያለበት የነጭ ሐር መጎናጸፊያ አላቸው ። ያለሱ ሥጋውና ደሙን አይፈትቱም ። ይህንንም በፅርዕ "አንዲሚንሲዮን" ይሉታል ። "ህየንተ ታቦት" ማለት ነው ። የሮማ ካቶሊኮች "ሜንሳ" ይሉታል ጠረጴዛ ማለት ነው ። ከዚህም ጋር እነሱ ከአምስቱ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በቀር አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚሠየምበት ጊዜ መንበሩ ላይ የዐፅመ ቅዱሳን ሽራፊ እንዲቀመጥበት ቀኖናቸው ያዝዛል" ብለው ዘግበዋል ።

ስለዚህ በዚህ አመለካከት ታቦት ወይም ሥርዓተ ታቦትም ባይኖር በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎች ነገሮችን ለመጠቀም ይቻላል ማለት ነው ። የግብጽ ወይም የቆብጥ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚጠቀሙበትን ሉሕ የተሰኘውን (ጽላተ ሠሌዳ) ስንመለከት አልፍሬድ ጄ በትለር "በግብጽ ጥንታዊ የቆብጥ አብያተ ክርስቲያናት " በተሰኘው መጽሐፋቸው ስለ አብያተ ክርስቲያኖች የመሰውያ ሥፍራ (Altar) አስመልክተው ግብጻውያን ይህንን ሥፍራ በሁለት ተምሳሌነት እንደሚመለከቱት ያብራራሉ ። አንደኛው የክርስቶስ መቃብር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእግዚአብሔር ዙፋን ነው ።

የመሠዊያው ሥፍራ በሸክላ ወይም በድንጋይ አራት ማዕዘን ሆኖ ይሠራል። በላዩ ላይ የመስቀል ቅርጽ የተሳለበት የእንጨት ጽላት ይደረጋል ። በዚሁ ጽላት ላይ አለፋና ኦሜጋ ይጻፍበታል በዙሪያውም IH XP YC OC ይባልበታል ። ይህ ደግሞ ከሮማውያን ወይም የላቲን አብያተ ክርስቲያናት አሠራር ጋር ተመሳሳይነት አለው ። ምክንያቱም በእነርሱ ዘንድ የተቀደሱት ዕቃዎች የሚቀመጡት አንድ የእንጨት ፥ የእምነበረድ ወይም የድንጋይ ጽላት በግድ መኖር እንዳለበት ያስገድዳሉና ።

ይህ የእንጨት ጽላት አቡነ ጎረጎሪዮስ "ሉሕ" ብለው የጠቀሱት መሆኑ ነው። ይህንን በተመለከተ በእንግሊዝ አገር የሚገኙት የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ የሆኑት አቡነ አንቶኒዮስ ሲገልጹ

እንዲህ ብለዋል " ሉሕ የአረቢኛ ቃል ሲሆን ጽላት ማለት ነው ። ጥቅሙም የመሠውያውን ሥፍራ ለመቀደስ ነው ። ቅባተ ሜሮን በማይገኝበት ሁኔታ በዚህ እንጨት አማከኝነት የመሠውያው ሥፍራ (Altar) ይቀደሳል" ። የዚህ እንጨት ቅርጽና በላዩ ያለው ስዕልና ጽሑፍ ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ዓይነት እንደሆነ ገልጸዋል ።

በመቀጠል ይህ ሉሕ ወይም ጽላተ ሠሌዳ ከሙሴ ጽላት ጋር (ማለትም ከብሉይ ኪዳን ታቦት ጋር) ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለውና እንዳልተያያዘ አስረድተዋል ። በእርሳቸው አገላለጽ የሥጋ ወደሙ መፈተትና ወይኑና ኅብስቱ ወደ ጌታችን ደምና ሥጋ የሚለወጠው "በሉሑ" ወይም በጽላተ ሠሌዳው አማካኝነት ሳይሆን "በጸሎት ፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት"እንደሆነ ገልጸዋል ።

ይህ እንደዚህ ከሆነ ፥ ማለትም የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓት ከሙሴ ጽላት ጋር ግንኙነት ከሌለው ሌሎቹንም የሙሴ ሕግጋት እንደዚሁም ምግብና የሰንበት አክብሮት በተመለከተ የቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት ምን ይሆን ? ለሚለው ጥያቄ ርኩስና ንጽሕ ምግብ የሚባል በክርስቲያኖች ዘንድ እንደሌለ ምግብ በስመ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ እስከተባረከ ድረስ የተባረከ እንደሚሆን አንደገናም ሰንበት በአዲስ ኪዳን እሁድ ማለትም ጌታ የተነሳበት ቀን እንደሆነም አብራርተዋል ። በመጨመርም በዕብራይስጥ ቋንቋ "ሳባት" ሲተረጎም ሰንበት፥ እረፍት ማለት ስለሆነ በጌታ ከሞት መነሣት ፥ ሞትን ድል በመንሳቱ ክርስቲያኖች እረፍት ያገኙበት ዕለት ስለሆነ እንደሚከበር አብራርተዋል ። በአጠቃላይም የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ከአይሁድ ባህል ወይም ከብሉይ ኪዳን የተወረሱ ደንቦችን የማትከተል እንደሆነ ገልጸዋል ።

Coptic Encyclopaedia በተሰኘ መጽሐፍ ላይ ስለ ግብጽ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የቁርባን ሥርዓት አፈጻጸም የተገለጸውን ስንመለከት ደግሞ ፥ በቁርባን ሥርዓቱ ወቅት በጥቅም ላይ ከሚውሉት እንደ ጽዋው ፥ የኅብስቱ ማስቀመጫ በእንግሊዘኛው ARK ተብሎ የሚጠራ ወይንም በአማሪኛው ስንተረጉመው "በታቦት" እንደሚጠቀሙ ይጠቅሳል ።

ይህ ታቦት መጠኑ 25 ሳንቲም በ25 ሳንቲም በ30 ሳንቲም ስፋትና ቁመት ያለው ሲሆን ሁልጊዜ መሰውያው/በመንበሩ መካከለኛ ሥፍራ መቀመጥ ያለበት ነው ። በታቦቱ ዙሪያ ጌታ ከመሰቀሉ በፊት ከደቀ መዛሙርቶቹ ጋር ራት ሲበላ የሚያሳይ ስእል ፥ የድንግል ማሪያም ፥ የአንድ መልአክ ስእልና እንደዚሁም ቤተ ክርስቲያኑ የተሰየመበት ጻድቅ በአራቱ ማዕዘን ዙሪያ ይቀመጣል ።

ይህ "ታቦት" ወይኑ የሚቀመጥበት የጽዋው ማስቀመጫ ነው ።

ይህንንም በእንግሊዘኛው ARK የሚለውን "ታቦት" በማለት የተረጎምኩት የሥርዓት ማስፈጸሚያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሚታወቀው ታቦት ወይም ጽላት ተብሎ ከሚጠራው ጋር በቅርጽም ሆነ በሥርዓት አጠቃቀም በፍጹም የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን ። በተጨማሪም ከፍ ሲል ከተጠቀሰው "ሉሕ" ከተሰኘውም የሥርዓት ማሳረጊያም ጋር ልዩነት እንዳለው ለመረዳት እንችላለን ።

ይህ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ከሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሥርዓትና ሕግጋት ከዚህ የተለየ በመሆኑ ብዙ ክርክሮችን ሊየሰነሳ ይችል ይሆን ? መሠረተ እምነቷን ከግብጽ በሚላኩላት ጳጳሳት አማካኝነት ያገኘች ኢትዮጵያ እንዴት ዓይነተኛ በሆነ ሥርዓትና ደንብ ላይ ልዩነት ሊገኝ ቻለ ? የመተዳደሪያ ደንቧን እንኳን ሳይቀር ከእስክንድሪያ የተቀበለች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በደንቦችና በቤተ ክርስቲያን አሠራር እንዴት ልዩነት ሊከሰት ቻለ ? እነዚህ ልዩነቶች ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር ብቻ ነው ከሌሎችም የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ጭምር ነው ?

በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ውስጥ ኢትዮጵያ ታላቅ ሥፍራ እንዳላት የታሪክ ተመራማሪዎችና የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በተደጋጋሚ ይናገራሉ ። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ 40 ጊዜ በላይ ተጠቅሶ መገኘቱ ነው ። በእርግጥ ኢትዮጵያ ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው ስያሜ ብዙ ክርክር ያስነሳ ነው ። ስምምነት ሊደረሽ የሚቻለው በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ተብላ በጂአግራፊ ክልል የምትታወቀውን አገርና እንደዚሁም ኤርትራን የሚያጠቃልል ለመሆኑ ጥርጥር የሌለው ሲሆን ነገር ግን ከዚያ በላይ ከግብጽ በስተደቡብ ያሉትን አገሮች ሊያጠቃልል የሚችል እንደሆነ ብዙ ሊቃውንቶች ይናገራሉ ። ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ተመራማሪዎች ለጥቁር አፍሪካ ሊሰጥ የሚችል ስያሜ ነው ብለው ይናገራሉ ።

ሌላው እግዚአብሔር በዘላለማዊው ዕቅድ ውስጥ ኢትዮጵያን እንዳካተታት ዓይነተኛ ማስረጃ የሚሆነው የክርስቶስ ወንጌል ወይም የክርስትና የምሥራች ቃል በመጀመሪያ ከደረሷቸው አገሮች ቀዳሚ ሥፍራ ይዛ መገኘቷ ነው ። በሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 26 ጀምሮ ስናነብ ታሪኩን እናገኘዋለን ። "የጌታ መልአክ ፊሊጶስን - ተነስትሀ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረበዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው ። ተነሥቶም ሄደ ። እነሆም ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ

በገንዘብዋም ሁሉ የሰለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳለወም መጥቶ ነበር ። ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር ። መንፈስም ፊሊጶስን - ወደዚህ ሠረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው ።

ፊሊጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማውና በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን? አለው እርሱም የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል ? አለው ። ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊሊጶስን ለመነው ። ያነበውም የነበረው የመጽሐፉ ክፍል ይህ ነበር ....” ይልና ጃንደረባው የኢሳያስ መጽሐፍ ምዕራፍ 53 ላይ ስለጌታ ኢየሱስ መስዋትነት የሚናገረውን ክፍል ያነብ እንደነበር ከገለጸ በኋላ ፊሊጶስ ይህንን ትንቢት መፈጸሙን ካስረዳው በኋላ ጃንደረባው በክርስቶስ አምኖ እንደተጠመቀ ያሳየናል ። በታሪክ እንደሚነገረው ደግሞ ይህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ወደ ኢትዮጵያ በደረሰ ጊዜ ንግሥቲቱንና የአገሬውን ሕዝብ ወደ ክርስትና እንደቀየረ ይነገራል።

እንግዲህ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ገባ ተብሎ የሚገመተው ወይም የሚታመነው አንደኛው መንገድ ይህ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች አዋቂዎች ክርስትና በእርግጥ ወደ ኢትዮጵያ ገባ ሊባል የሚቻለው በ4ኛው ክፍለ ዘመን በአባ ሰለማ ከሳቴ ብርሃን አማካኝነት እንደሆነ ያምናሉ ። ይህ ሆነም ያ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ቀደም ብሎ እንደሆነ እንረዳለን በሌላ በኩል ደግሞ እንደሌሎቹ የክርስትና ትምህርት እንደተሰበከባቸው አገሮች እምነቱ ከኢየሩሳሌም በተነሳው እንቅስቃሴና ትምህርት መሠረት መሆኑ ግልጽ ነው ።

ምንም እንኳ የክርስትና ሃይማኖት የመጀመሪያ ተከታዮች አይሁዶች (ወይም በእሥራኤላውያን) ቢሆኑም ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ላይ ተጽፎ እንደምናገኘው ክርስትና የአይሁድ ሥርዓትን የሚጠቀልል ወይም የሙሴ ሕግን የሚጠቀልል ሥርዓት ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህረት ላይ የተመሠረተ አዲስ ሕይወትንና አዲስ ጅማሬን የሚያበስር ትምህርት እንደነበር ለመረዳት ይቻላል። ይህንን ጉዳይ በደንብ ለመከታተል ሁለት መንገዶችን መመልከት ይቻላል ። አንደኛው ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘውን ማስረጃ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከታሪክ ማህደር ልናገኝ የምንችለውን ማስረጃ ነው። የታሪክ ማስረጃዎቹን በመጀመሪያ እንዳስስና ከዚያ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንዞራለን ።

በታሪክ ማህደር እንደምንረዳው ክርስትና ከእየሩሳሌም ከተማ ወጥቶ ወደ ተለያየ ክፍል በተስፋፋ ጊዜ ብዙውን የዓለም ክፍል

ይገዛና ያስተዳድር የነበረው የሮም መንግሥት ነበር ። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ተመላልሶ አገልግሎቱን በፈጸመ ጊዜም እስራኤልና በዙሪያዋ የነበሩት አገሮች ሁሉ በሮም መንግሥት ግዛት ሥር ነበሩ ።

በዚህም መንግሥት መመሪያ መሠረት ማንኛውም ሃይማኖት በመንግሥት መታወቅና መመዝገብ እንደነበረበት ይታወቃል ። በዚሁ መሠረት የአይሁድ ሃይማኖት በመንግሥት የታወቀ ነበር ። ክርስትናም በመንግሥት ደረጃ ከአይሁድ ሃይማኖት ክፍል አንድ ዘርፍ ሆኖ ይገመት ስለነበር በመንግሥት ደረጃ ለአይሁዶች የሚሰጥ የነበረው ጥበቃ ለክርስቲያኖችም ይሰጥ ነበር ።

ይህ ሁኔታ እስከ 64 ዓም እንደዚሁ ቀጥሎ እስከዚህ ጊዜ ድረስ በመንግሥት በኩል የተቀነባበረ አንድም ስደት ወይም መከራ በክርስቲያኖች ላይ አልደረሰባቸውም ። ለመጀመሪያ ጊዜ በክርስቲያኖች ላይ በመንግሥት እጅ ስደት የተጀመረው በ64 ዓም በንጉሥ ኔሮ አስተዳደር ጊዜ በሮም ከተማ ትልቅ የእሳት ቃጠሎ ደርሶ ክርስቲያኖች በዚህ ጉዳይ ተጠርጥረው ስደትና መከራ እንደደረሰባቸው ታሪክ ይዘግባል ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ግን ክርስቲያኖች ተቃውሞ ይደርስባቸው የነበረው ከአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮችና የሃይማኖት አስተማሪዎች ዘንድ ብቻ ነበር ።

ችግርና ተቃውሞ የደረሰባቸውም ያስተምሩ በነበረው ትምህርት ምክንያት ነበር ። አይሁዶቹ ኢየሱስ ክርስቶስ በነርሱ ትንቢት መሠረት የሚጠበቀው መሲሕ ነው ብለው ለማመን እና ለመቀበል አልቻሉም ። እነርሱ መሲሑ ከዳዊት ዘር ከንጉሣዊ ቤተሰብ መወለድ አለበት ብለው ይጠባበቁ ነበርና ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከድሀ ቤተሰብ በበረት ስለተወለደ እንዴት እርሱ መሲሑ ሊሆን ይችላል ባዮች ናቸው ። ከዚህ ሌላ መሲሑ መንግሥት በመገልበጥ ድል ለማድረግና ለመንገሥ እንጂ ለመሞት አይደለም የሚመጣው ብለውም ነበር የሚጠብቁት ። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል የእርግማን ሞት በመሞቱ እርሱ መሲሑ ሊሆን አይችልም የሚል ተቃራኒ አስተያየት ነበራቸው ። ስለዚህም የክርስትናን ትምህርት እየሰበኩ ይዞሩ የነበሩት አስተማሪዎችን አይሁዶቹ በጥብቅ ይቃወሙ ነበር ። ይህ ተቃውሞ ብዙም ሳይቆይ ፥በሐዋሪያት ዘመን እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስን ከፍተን የሐዋሪያት ሥራን በምናነብበት ጊዜ ለመረዳት እንችላለን ።

ለዚህ ጽሑፍ የሚረዳውና ግንኙነት ያለው ግን አይሁዶቹ ክርስቲያኖቹን የሙሴን ሕግ ባለመጠበቃቸው ምክንያት ያስነሱት ተቃውሞ ነው ። ይህም የሰንበት መከበር ፥ ግዝረት ፥ ቅዱስና እርኩስ

መብልን ሌሎችም በሙሴ ሕግ መሠረት መጠበቅ የሚገባቸው የነበሩ ሥርዓቶችን የተመለከተ ነው ። ይህ ቅራኔ ክርስትና ከኢየሩሳሌም ወጥቶ በአረማውያን ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ በመጣ ጊዜ እየሰፋ እንደመጣ ለመረዳት ይቻላል ። ከጊዜ በኋላም ክርስቲያኖች ወደ ምኩራብ እንዳይገቡ እንደተከለከሉ የታሪክ ዘጋቢዎች ይናገራሉ ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘውን ማስረጃ በምንመረምርበት ጊዜ ደግሞ ተመሳሳይ ተቃውሞ በክርስቲያኖች ላይ ደርሶ እንደነበር እንረዳለን ። የዲያቆኑ የእስጢፋኖስ በድንጋይ መወገር ፥ የጴጥሮስ መታሰር ፥ ሌሎችም አይሁዳውያን በክርስቲያኖች ላይ ባስነሱት ተቃውሞ ምክንያት የመጡ እንደሆነ እናውቃለን ። ሐዋሪያቶችም ቢሆኑ አይሁዳውያን ስለነበሩና ሥርዓቱን ከጥንት ጀምሮ ይከተሉ ስለነበር ከክርስትና ትምህርታቸው ጋር ሲጋጭባቸውና ጥርጣሬ ላይ ሲደርሱ እንመለከታለን ። ለምሳሌ ጴጥሮስ ከአረማውያን ጋር አብሮ ሲበላ ቆይቶ ከኢየሩሳሌም አጥባቂ የነበሩ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ወደ ከተማው በመጡ ጊዜ ከእነርሱ ጋር በመተባበር ከአረማውያን ጋር አልበላም በማለቱ ጳውሎስ እንደተቃወመውና እንደገሰጸው ተጽፎ እናገኛለን ።

ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህንን የአይሁድ ሥርዓት በመጠበቅ ረገድ ይነሳ የነበረውን አመለካከት በጥብቅ እንደተቃወመ በጻፋቸው መልዕክቶቹ በግልጽ እና በሰፊው ተተንትነው እናነባለን ። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ መፍትሔ ለማግኘት ሲባል በኢየሩሳሌም ተሰብስቦ የነበረውም የመጀመሪያው የሐዋሪያት ጉባዔ የደረሰበት ውሳኔም ይኸው ነበር ። የውሳኔው ሙሉ ቃል እንዲህ ይላል “ ሐዋሪያትና ሽማግሌዎች ወንድሞችም በአንጾኪያና በሶሪያ በኪልቅያም ለሚኖሩ ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ ወንድሞች ሰላምታ ያቀርባሉ ። ያላዘዝናቸው ሰዎች ከእኛ ወጥተው ትገረዙ ዘንድና ሕግን ትጠብቁ ዘንድ ይገባችኋል ብለው ልባችሁን እያወኩ በቃል እንዳናወጡአችሁ ስለ ሰማን ስለ ጌታችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነፍሳቸውን ከሰጡት ከምንወዳቸው ከባርናባስና ከጳውሎስ ጋር የተመረጡትን ሰዎች ወደ እናንተ እንልክ ዘንድ በአንድ ልብ ሆነን ፈቀድን ። እራሳቸውም ደግሞ በቃላቸው ያንኑ ይነግሩአችሁ ዘንድ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል ። ለጣዖት ከተሰዋ ከደምም ከታነቀም ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ ። ጤና ይስጣችሁ” ። (ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ቁጥር 23 – 29) ።

እንግዲህ የክርስትና መስፋፋትና መስራጨት ፥ ከአይሁድም ሥርዓት ጋር የነበረው ቀረቤታ ይህንን ይመስላል ። እነዚህን ሐሳቦች መመልከት ያስፈለገበት ምክንያት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ በገባ ጊዜ ምን ትምህርትን ያጠቃለለ እንደሆነ ለማየት እንዲረዳን ነው ። ክርስትና በጃንደረባው አማካኝነት ነው የገባው ብለን ካመንን ፊሊጶስ ክርስቶስ ኢየሱስ ይጠበቅ የነበረው መሲሕ እንደሆነና ምን እንዳስተማራቸው ፥ የሞቱንና የትንሳኤውን ተአምራት ፥ ሌሎችም ያደረጋቸውን ተአምራት ፤ እንደዚሁም በጴንጤቆስጤ ዕለት መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደወረደ አሁን ደግሞ ሐዋሪያት ምን እያስተማሩና ምን እያደርጉ እንደሚገኙ ፤ የኢየሱስ ክርስቶስም ትዕዛዝ "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ ወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" የሚለውን ከነገረው በኋላ ሳይሆንም አይቀርም ጃንደረባው የተጠመቀው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ክርስትና በ4ኛው ክፍለ ዘመን በፍሬሚናጦስ ወይም በአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በኩል ነው የገባው ብለን ካመንን በተመሳሳይ ሁኔታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ፥ የሰውን ኃጢአት ለማስተሰረይ በሰው ምሳሌ ተገልጾ በእሥራኤል አንደተመላለሰ ፥ በአገልግሎቱም ዘመን ብዙ ተአምራትን እንዳደረገ እያስተማሩ ወንጌልን እየሰበኩ አስተምረው መሆን አለበት ብለን መቀበል ይኖርብናል ።

በመጀመሪያውም ሆነ በሁለተኛው አመለካከት መሠረት ኢትዮጵያ ቀድሞም የአይሁድ ሥርዓት ትከተል ስለነበር ሥርዓቶቹን ክርስቲያናዊ ይዘት እየሰጠቻቸው በዚያው ቀጠለችባቸው ልንል እንችላለን ። በዚህም አመለካከት መሠረት ታቦቱ ይገኝ የነበረው በኢትዮጵያ ስለነበር ጃንደረባው ይዞት ከመጣው ትምህርት ጋር በመያያዝ ሥርዓቱ ቀጠለ ማለት ነው ።

ነገር ግን ይህ ሥርዓት ከኢየሩሳሌም የተላለፈ የሐዋርያት ተውፊት እንዳልሆነ ለመረዳት ይቻላል ። በመጀመሪያ ደረጃ ሐዋርያት ወይንም የመጀመሪያ ክርስቲያኖች በታቦት ዙሪያ ክርስቲያናዊ ወይም አይሁዳዊ ይዘት ያለው ሥርዓት አልነበራቸውም ፥ ሊኖራቸውም አይችልም ። ምክንያቱም ታቦት በዚያን ወቅት በእሥራኤል ፥ በቤተ መቅደሱ ስላልነበረ ። ለዚህም ነው ክርስቲያናዊ የታቦት ሥርዓት ከብሉይ ኪዳን ጋር በተያያዘ ከኢትዮጵያ አርቶክስ ቤተ ክርስቲያን በስተቀረ በሌላ አብያተ ክርስቲያን ውስጥ በፍጹም ሊገኝ የማይቻለው ። (የታቦት ሥርዓት

አሁንም በአይሁዶች ዘንድ በየምኩራባቸው synagogues ውስጥ የለም) ፡፡

ታዲያ ይህ እንዲህ ከሆነ ታቦት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የግድ አስፈላጊ ነው ፤ ያለ ታቦት ቤተ ክርስቲያን ሊኖር አይችልም ለማለት አይቻልም ፡፡ ምክንያቱም በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ፥ ከዚያም በየከተማዎቹ በአንጾቂያ ፥ በቆሮንቶስ ፥ በሶሪያ ፥ በኤፌሶን ፥ በገላቲያ ፥ በተሰሎንቄ ፥ በሌላም ሌላም ፤ በሐዋርያቱ እየተመሠረቱ የክርስቶስን የምሥራች ወንጌል ይሰብኩና ያስተምሩ በነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ታቦት ባለመኖሩ ነው ፡፡ ያለ ታቦት ቤተ ክርስቲያን አይመሠረትም ከተባለ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ቤተ ክርስቲያኖችና እንዲሁም በአሁኑ ጊዜም በተለያዩ አገሮች እና አህጉሮች የተመሠረቱት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክስርቲያን በስተቀር ሌሎችንም (የምሥራቅ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያኖችን ጨምሮ በሙሉ ቤተ ክርስቲያን ተብለው ሊጠሩ ወይም ትክክለኛ የአምልኮ ሥርዓት አያካሂዱም ማለት ይሆናል ይህ ደግሞ አስቸጋሪ ነው ፡፡

በተመሳሳይ · ሁኔታ ቀደም ሲል የታቦት ሥርዓት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተመለከትን ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ አቋም ታቦቱ ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት ሥፍራ እንደሆነና በታቦቱ ላይ በሚደረገው ጸሎት ኅብስቱ ወደ ጌታ ሥጋ ወይኑ ደግሞ ወደ ጌታ ደም የሚለወጥበት እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ይህ እንዲህ ከሆነ ቀደም ሲል ለምሳሌነት የጠቀስናቸው አብያተ ክርስቲያናት የታቦቱ ሥርዓት ስላልነበራቸው የቁርባን ሥርዓታቸው ከዚህ የተለየ ነበር ማለት ነው ፡፡

ይህ ደግሞ የሚያመለክተው የቁርባን ሥርዓት መሠረተ ሃሳቡ ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የመጣ ቢሆንም (ማለትም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋሪያቱ በዕለተ ሐሙስ ካስተማራቸውና ይህንን ደግሞ ማለትም ሥርዓቱን ሁልጊዜ እንዲያደርጉት ካሳሰባቸው በኋላ) አፈጻጸሙ ግን የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን ፡፡ ስለዚህም ከሐዋርያት አንስቶ ያለ ተውፊት ነው ለማለት አይቻልም ፡፡

የቁርባን ሥርዓትን ካነሳን ዘንዳ አንድ ሳንመለከተው ማለፍ የሌለብን ጉዳይ አለ ፡፡ ይኸውም ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ሐሙስ ለደቀመዛሙርቱ የቁርባንን ሥርዓት ሲያስተምራቸው በአይሁድ ባሕል መሠረት የፋሲካን የቂጣ በዓል ለማክበር ተሰብስበው በነበረበት ገበታ ላይ ነበር ፡፡ በማርቆስ ወንጌል

ላይ ስናነብ ምግቡን መብላት ከጀመሩ በኋላ እንደነበረም ማስተዋል ይቻላል ። ይህንን በመከተል በመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች የቁርባን ሥነ ሥርዓት ዛሬ እንደሚደረገው ሳይሆን ወደ ማምሻው ላይ ምእመናን በገበታ ዙሪያ ተሰብስበው በመብላት የሚያደርጉት ሥርዓት ነበር ። ይህ በታሪክ የተዘገበ ሲሆን ከመጽሐፍ ቅዱስም ማስረጃ ሊገኝለት የሚችል ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው የመጀመሪያው መልዕክቱ ስለ ብዙ ነገር እያነሳ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ 'የተከሰተውን የተዛባ አመለካከት ፥ ይታይ የነበረውን ጥፋት እየጠቀሰ ሲያርምና ሲገስጽ እንዲሁም ሲመክር ካነሳቸው ጉዳዮች አንዱ የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት አንደነበር 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 20 ጀምሮ ያለውን ስናነብ እንረዳለን ። እንደዚህም ብሎ ይላቸዋል " እንግዲህ አብራችሁ ስትሰበሰቡ የምትበሉት የጌታ ራት አይደለም በመብላት ጊዜ እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላልና አንዱም ይራባል አንዱ ግን ይሰክራል ። የምትበሉባቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር ትንቃላችሁ አንዳችም የሌላቸውን ታሳፍራላችሁን ? ምን ልበላችሁ ? በዚህ ነገር ላመሰግናችሁን ? አላመሰግናችሁም ። ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመስገነ ቆርሶም እንካችሁ ብሎ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ ። እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንስቶ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ ።

ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና" ይልና በመቀጠል ለሥርዓቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ካስረዳቸው በኋላ በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 33-34 ላይ " ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ ለመብላት በተሰበሰባችሁበት ጊዜ እርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ ። ማንም የራበው ቢኖር ለፍርድ እንዳትሰበሰቡ በቤቱ ይብላ ። የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ" ይላቸዋል ።

እንግዲህ በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው ሥርዓቱ በገበታ ዙሪያ የሚፈጸም ነበር ። ስቱአርት ጂ ሆል የተሰኙ በሎንዶን በኪንግስ ኮሌጅ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፕሮፌሰር የነበሩ Doctrine and Practice in the Early Church በተሰኘው መጽሐፋቸው ይህንኑ አስመልክተው ሲጽፉ እስከ 200 ዓ ም ገደማ የቁርባን ሥርዓት በገበታ ዙሪያ ምግብ በመመገብ መልክ እንደነበረ ገልጸው እያንዳንዱ ግለሰብ ያለውን

እያዘጋጀ አምጥቶ በጋራ አብሮ የሚካፈልበት ገበታ እንደነበረ ዘግበዋል ::

በኋላም እየቆየ ሲሄድ ወደ 3ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ገደማ ላይ የቁርባኑ ሥርዓት በወይንና በኅብስቱ ብቻ ተወስኖ የገበታው ሥርዓት ለብቻው ተለይቶ “አጋፔ” (Agape Feast - የፍቅር ገበታ) እየተባለ ይደረግ እንደነበረም አያይዘው አስፍረዋል ::

እንግዲህ እስካሁን በዳሰስናቸው ነጥቦች መሠረት ልንረዳ የምንችለው ነገር አንደኛ ታቦቱ በክብረ ነገሥት ዘገባ መሠረት ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ተሰርቆ በንጉሥ ምኒሊክ ቀዳማዊ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላ ሕዝቡ አብሮት ከመጡት የእሥራኤል ካህናት በተማረው መሠረት የአይሁድን ኑሮና የሃይማኖት ሥርዓቶች እየፈጸመ የቆየ ስለነበር ክርስትና ወደ አገሪቱ በገባ ጊዜ እነዚህን ባሕሎች ወይም ሥርዓቶች ወደ ክርስትና ይዘት እየለወጠ መቀጠሉ ግልጽ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን :: ስለሆነም የታቦት ሥርዓትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በራሷ አነሳሽነት እንደሆነ እንጂ ከማናቸውም ከእርሷ በፊት የክርስትናን ሃይማኖት ተቀብለው ከነበሩት አማኞች ያገኘችው ወይም ከነዚህ የተላለፈላት ተውፊት እንዳልሆነ ግልጽ ነው :: ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ሥርዓቱ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አለመገኘቱ ነው ::

በሁለተኛ ደረጃ የታቦቱን ሥርዓት አስመልክቶ በተለይም የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓት በተመለከተ ያለታቦቱ ሥጋ ወደ ደሙ ሊፈተት አይችልም ለማለት አስቸጋሪና የሌሎቹን የክርስትና ሃይማኖት ክፍሎች ሥርዓት ውድቅ የሚያደርገው ስለሆነ ጥያቄ ላይ የሚያደርስ ይሆናል :: ለምሳሌ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተመሳሳይነት ያላትን የግብጽን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን (ቆብጥን) ብንወስድ ቀደም ሲል ለመመልከት እንደቻልነው ከአባ ጎርጎሪዮስ መጽሐፍ በመነሳት ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ የቁርባን ሥርዓትና ስለሚጠቀሙበት “ሉሕ” ባየንበት ጊዜ ከታቦተ ጽላት ጋር የሚመሳሰል ቢመስልና ትርጉሙም እንኳ ጽላት ማለት ቢሆንም ከአይሁዳውያን የቃል ኪዳን ታቦት ጋር ግንኙነት የሌለው እንደሆነ ተመልክተናል::

ከዚህ በተረፈ በአይሁድና በክርስትናው ሥርዓት መካከል የቃል ኪዳኑን ታቦት በተመለከተ ብዙ ልዩነት እንዳለውም ለማየት ችለናል :: እነዚህን ሐሳቦች ሁሉ ከግንዛቤ በማስገባት ስናጠና በግልጽ የሚታየው እና የምንደርስበት ማጠቃለያ አንድ ነው :: እርሱም በንግሥት ሳባና በልጇ በምኒልክ ዘመን የቃል ኪዳኑ ታቦት

ከኢየሩሳሌም ተሰርቆ ከመጣበት ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያ የአይሁድ እምነት ፥ ባህል ፥ ሥርዓት ትፈጽም ስለነበረ፥ በታቦቱ ዙሪያም የታዘዙትን ሥርዓቶች ሁሉ ያደርግ ስለነበር ክርስትና ወደ አገሪቱ ሲገባ እነዚህን ሥርዓቶች ፥ ባህሎችና ደንቦች ክርስቲያናዊ ትርጉም እየተሰጣቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል ጀመሩ የሚል ይሆናል ። በዚህም አመለካከት መሠረት የቃል ኪዳኑ ታቦት በአገሪቱ ስለነበረ ክርስትና በሐዋርያት ዘመን በጃንደረባው አማካኝነትም ሆነ ቆይቶ በአባ ሰላማ አማካኝነት ከአክሱም እምብርት ወደ የከተማው ሲስፋፋ ካህናት ሥርዓቱን አስፋፍተውታል ማለት ነው ። ይህንን ማጠቃለያ እንደዚሁ በቀላሉ ለመቀበል ግን የሚያስቸግሩ ጉዳዮች አሉ ።

በመጀመሪያ ደረጃ ልንመለከተው የሚገባን ጉዳይ በብሉይ ኪዳን በአሪት ዘጸአት ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተቀርጸ አስቀድሞ በድንኳን ውስጥ በኋላም በመቅደስ ውስጥ ተቀምጦ የኃጢአትና የአምልኮ ሥርዓት ሲከናወንበት የቆየውን የታቦት ቅርጽና አሠራር በኢትዮጵያ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለምዶ አነጋገር ታቦት ተብሎ የሚጠራውን ጽላትና በዙሪያው የሚደረገውን የአምልኮት ሥርዓት በማገናዘብ የምናገኘው ልዩነት ነው ።

አሁን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሚገኘው ሥርዓት ተነስተን ወደኃላ በምንመለከትበት ጊዜ የቃል ኪዳኑ ታቦት በአክሱም ከተማ ይገኝ ከነበረና እንደ አይሁድ ደንብና ሥርዓት* በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ተቀምጦ ሊቀ ካህኑ በዓመት አንድ ጊዜ የእንስሳ ደም ይዞ እየገባ የኃጢአት ማስተሰሪያ ሥርዓት ከነበርና ፣ ክርስትና ሲገባ እና ካህናቱም ሆኑ ሕዝቡ ይህንን አዲስ እምነት ሲቀበሉ ፣ እንግዲህ ክርስቶስ ኢየሱስ ለአንዴም ለመጨረሻም ጊዜ የበግ ወይም የፍየሎች ደም ይዞ ወደ እግዚአብሔር በማያዳግም ሁኔታ ገብቷል እና ከእንግዲህ ወዲህ የማስተሰሪያ ሥርዓት ደም መርጨት አያስፈልግም በማለት ካህናቶቹ የደም ስርየት ሥርዓቱን በማቆም በምትኩ የመስዋዕቱ ምሣሌ የሆነውን የሥጋ ወደሙ/ቅዱስ ቁርባን ሥርዓት በታቦቱ ዙሪያ በማከናወን ይቀጥላሉ ማለት ነው ።

ይህ ሥርዓት ክርስትና በደረሰበት እና በተስፋፋበት ከተማ ሁሉ እንዴት ሊመሠረት እንደሚችል ስንገምት ከአክሱም በሚወጣ ትዕዛዝ በዚያ በሚገኘው በንግሥት ሳባና በልጁ በቀደማዊ ምኒሊክ ዘመን የመጣውን የቃል ኪዳኑን ታቦት በሚመስል ሁኔታ ተመሳሳይ ታቦት እየተዘጋጀ በዙሪያው የአምልኮው ሥርዓት እንዲከናወን እና ያለ

ታቦቱ በምንም ዓይነት የሥጋ ወደሙ ሥርዓት እንዳይፈጸም ጥብቅ የሆነ መመሪያ እየተሳለፈ የታቦቱ ቅርጽ ለመሥራት እንዲቻል የፕላን መመሪያ መተላለፍ ይኖርበታል ። ነገር ግን ይህ እንዳልሆነ ቀደም ባለው የመጽሐፉ ክፍል በብሉይ ኪዳን/በአይሁዳውያን የታቦት ቅርጽና ምስል እና ዛሬ በኢትዮጵያ በሚገኘው የታቦት ቅርጽና ምስል እንደዚህም አጠቃቀም ያለውን ልዩነት ለመመልከት በሞከርን ጊዜ የዳሰስነው ግልጽ ያደርገዋል ።

በአሁኑ ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ ያለው ጽላት እንጂ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ታቦት በውስጡም አሥርቱ ቃላት የተጻፈበትን ሁለት ጽላቶች እንደሌሉ ግልጽ ነው ። ከዚህ በተረፈ በብሉይ ኪዳን መሠረት ታቦትን በየቤተ ክርስቲያኑ በመቅረጽ ለማስቀመጥ ፥ በንጹሕ ወርቅ መለበጥ ስለሚያስፈልገው እንደዚሁም የታቦቱ ክዳን (የማስተሰሪያው ክዳን) ከነኪሩቤሎቹ ከንጹሕ ወርቅ ብቻ መሠራት ስላለበት የማይቻል ነው ።

ይህ እንደዚህ ከሆነ ከአክሱም እየተስፋፋ የሄደውን ሥርዓት ከዚህ በተለየ መሆን አለበት ማለት ነው ። ስለሆነም ከፍ ሲል የተመለከተውን ማጠቃሊያ ውድቅ ያደርገዋል ። በሁለተኛ ደረጃ ልንመልሰው የሚገባን ዓቢይ ጥያቄ - ታዲያ ለምን የአይሁድ ባህልና ሥርዓት ይፈጽሙ የነበሩት በእሥራኤልም ሆነ በስደት የነበሩት አይሁዳውያን በኋላ ወደ ክርስትና ሲመለሱ ይህንኑ ማለትም የታቦት ሥርዓት እንኳ ባየሆን በብሉይ ኪዳን የሚገኙትን ሕግጋት ወይም ሥርዓቶች በአጠቃላይ አልፈጸሙም ? የሚል ይሆናል። የአንዳንድ ግለሰቦች መልስ/አስተያየት - አይ እነርሱ እራሳቸው ንቀውት ትተውት ይሆናል እንጂ መፈጸም ወይም ሥርዓቱ መቀጠል አለበት የሚል ይሆናል። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ በተለይም ጳውሎስ ለገላቲያና ለሮሜ ሰዎች በጻፋቸው መልዕክቶች ላይና እንደዚሁም በዕብራውያን መልዕክት ላይ ይህንን በግልጽ የሚቃረኑ ሆነው ይገኛሉ ።

በነዚህም ምንባቦች መሠረት ንቀውት ሳይሆን የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች በሙሉ ምሳሌአዊ የነበሩ ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ እንደሞግዚትነት ያገለግሉ የነበሩ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የማያስፈልጉ ናቸው ብለው ስላመኑባቸው እንደሆነ እንረዳለን ።

ይህንን በግልጽ ለማሳየት ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦችን መጥቀስ አስፈላጊ ይሆናል ።

"ሕጉ ፍጹም አላደረገምና ስለዚህም የምትደክም

የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትዕዛዝ ተሽራለች ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት የተሻለ ተስፋ ገብቶአል " ዕብራውያን 7 ፤ 18-19

"ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና...." ዕብራውያን 10 ፤ 1

"ወንድሞች ሆይ እንደ ሰው ልማድ እላለሁ ። የሰው ስንኳ ቢሆን እርግጠኛውን ኪዳን ማንም አይንቅም ወይም አይጨምርበትም ። ለአብራሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ ። ስለ ብዙዎችም እንደሚነገር - ለዘሮቹም አይልም ስለ አንድ እንደሚነገር ግን - ለዘርህም ይላል እርሱም ክርስቶስ። ይህንም እላለሁ ከአራት መቶ ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተረጋገጠውን ኪዳን የተስፋውን ቃል እስኪሽር ድረስ አያፈርስም ርስቱ በሕግ ቢሆንስ እንግዲያስ በተስፋ ቃል አይሆንም በተስፋ ቃል ግን እግዚአብሔር ለአብራሃም ሰጥቶታል ። እንግዲህ ሕግ ምንድር ነው ? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ በመካከለኛ እጅ በመላእክት በኩል ስለ ሕግ መተላለፍ ተጨመረ ። መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ግን አንድ ነው ። እንግዲህ ሕግ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን ? አይደለም ። ሕያው ሊያደርግ የሚቻለው ሕግ ተሰጥቶ ቢሆንስ ኖሮ በእውነት ጽድቅ ከሕግ በሆነ ነበር ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተስፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል ። እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠብቅ ነበር ። እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም" ። ገላቲያ 3 ፤ 15-25

በእነዚህ ጥቅሶች ላይ በአብዛኛው ጊዜ የሚሰነዘረው ምላሽ ጥቅሶቹ የሚያመለክቱት የመስዋዕት ሕጎችን እንጂ ሌላ ነገር አይደለም የሚለው ነው ። እውነት ነው የመስዋዕት ሕግን ያጠቃልላል ። ነገር ግን ቀረብ ብሎ ለተመለከተው በብሉይ ኪዳን ውስጥ

ለእሥራኤላውያን የተሰጡት ሕግጋት ቁጥራቸው እጅግ በጣም ብዙ እና አንዳንድ ጊዜ የማናስተውላቸው መሆናቸውን ማየት ይቻላል ፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በመጽሐፈ ሌዋውያን ተጠቅሰው የምናገኛቸው ሕግጋት በጣም ብዙ ናቸው ፡፡

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሙሴ ሕግ ብሎ ሲጠቅስ እንዚህን በሙሉ ሕግጋት እንደዚሁም የመሥዋዕት ሥርዓቱን ሁሉ ጨምሮ ፥ በአዲስ ኪዳን ላይ በዝርዝር የተጠቀሱትን እንደ ግዝረት ፥ እርኩስና ቅዱስ መብል ፥ ሰንበት ወዘተ.... የሚያካትት ነው ፡፡ እነዚህ የመስዋዕት ሕግጋት ቢሆኑም የሚፈጸሙት በታቦቱ ዙሪያ ነው ፡፡ ታቦቱ እና መቅደሱ በሌሉበት ሥፍራ እነዚህን በሙሴ በኩል ከእግዚአብሔር የተሰጡትን ሕግጋት ለመፈጸም አይቻልም፡፡

በነዚህ ሁለት ትንታኔዎች መሠረት የምንደረስበት ነጠብ አንድ ነው ፡፡ ይኸውም በብሉይ ኪዳን የሚገኘው የታቦት ሥርዓት ወደ ክርስትና የተለወጠው በኢትዮጵያ ብቻ ሲሆን ይህንንም አቡነ ጎርጎርዮስ ሲጽፉ እንዲህ ብለዋል “ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ... ከክርስትና በፊት የብሉይ ኪዳን አገር የነበረችው ኢትዮጵያ በክርስትና ጊዜም ከብሉይ ኪዳን ያገኘቻቸውን ጠቃሚ ነገሮች በክርስትና መንፈስ እየተረጎመች ትጠቀምባቸዋለች ፡፡ ከብሉይ ኪዳን ከወሰደቻቸው አንዱ ጽላተ ኪዳን ታቦተ ሕግ ነው” ፡፡ በእርሳቸው አባባል የዚህ ሥርዓት መተርጎም በራሷ (በቤተ ክርስቲያኒቱ) ወይም በኢትዮጵያውያኖች አነሳሽነት እንደሆነ የሚያመለክት መሆኑ ነው ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ ያለው ሳይሆን ስናደርግ የነበረውን አዲስ መንፈሳዊ ትርጉም ሰጥተን እንቀጥላለን የሚል አመለካከት የያዘ ነው ማለት ነው፡፡

ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ያለው ቢሆን ኖሮ በሌሎችም አብያተ ክርስተያነት ዘንድ ይህ ሥርዓት ይታይ ነበር ፡፡ አሁን ግን እንደዚህ እንዳልሆነ በገልጽ ሊታይ የሚችል ክስተት ነው ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳ ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በምናነብበት ጊዜ ቅራኔ ሊፈጥር የሚችል ይመስላል፡፡ ለዚህ ቅራኔ በተለይም በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል የማደሪያውን ድንኳን፥ የመስዋዕት ሥርዓት ዝርዝር ፥ ታቦቱን ጨምሮ ሌሎችንም የአምልኮ ቁሳቁሶች ጠቅሰን ከተነጋገርንባቸው ጉዳዮች ጋር ስናገናዝበው ቅራኔው የሰፋ ይሆናል ፡፡

ምንባቡ እንዲህ ይላል ፤

“ፊተኛዪቱም ደግሞ የአገልገሎት ሥርዓትና የዚህ ዓለም የሆነው መቅደስ ነበራት ፡፡ የመጀመሪያይቱ ድንኳን

ተዘጋጅታ ነበርና በእርሷም ቅድስት የምትባለው ውስጥ መቅረዙና ጠረጴዛ የመሥዋዕቱም ኅብስት ነበረባት ከሁለተኛውም መጋረጃ ወዲያ ቅድስተ ቅዱሳን የምትባለው ድንኳን ነበረች ፤ በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ ሁለንትነዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ ፥ በላይዋም ማስተሰሪያውን የሚጋርዱ የክብር ኪሩቤል ነበሩ ስለ እነዚህም ስለ እያንዳንዳቸው ልንናገር አሁን አንችልም ፡፡ ይህም እንደዚህ ተዘጋጅቶ ሳለ ........ ፊተኛይቱ ድንኳን በዚህ ገና ቆማ ሳለች ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል ፡፡ ይህም ለአሁኑ ጊዜ ምሳሌ ነው እንደዚህም መባና መሥዋዕት ይቀርባሉ እነዚህም እስከ መታደስ ዘመን ድረስ የተደረጉ ስለ ምግብና ስለ መጠጥም ስለ ልዩ ልዩ መታጠብም የሚሆኑ የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ናቸውና የሚያመልከውን በሕሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም ፡፡

ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ሳለው መልካም ሊቀ ካህናት ሆኖ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም ፡፡ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱት ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንጻት የሚቀደሱ ከሆኑ ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞት ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን ?

ዕብራውያን 9፤ 1-14

በተመሳሳይ ሁኔታ ጠቅላላው ሐሳቡ አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን የሚሻል እንደሆነና ፍጹምነትም እንዳለው የሚያሳይ ክፍል በሌላ ሥፍራ "አሁን ግን በሚሻል ተስፋ ቃል በተመሠረተ በሚሻል ኪዳን ደግሞ እጅግ የሚሻል አገልግሎት አግኝቶአል ፡፡ ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው ለሁለተኛው ስፍራ ባልተፈለገም ነበር ፡፡ .....አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቶአል አሮጌና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል" (ዕብራውያን 8 ፤ 6 እና 13)፡፡

እነዚህ ከላይ የተመለከታናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

በተለይም በመጀመሪያው ጥቅስ የተሰመረበት ክፍል እንደሚያሳየው በብሉይ ኪዳን በማደሪያው ዙሪያ ይደረግ የነበረው የመስዋዕት ሥርዓትና አገልግሎት ሁሉ እስከ ዘመን መታደስ ድረስ እንደነበረ ያሳያል ። ይህ የመታደስ ዘመን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ ራሱን መስዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እስካቀረበበት ዘመን ድረስ ያለውን የሚያመለክት ነው ። ስለዚህም የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ለአንባቢዎቹ ለማስተላለፍ የሚፈልገው መልዕክት እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለሕዝቡ ሰጥቶት የነበረው ሥርዓት ምሳሌ ነበር አሁን ግን የዛ ምሳሌ አካል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተገለጠ ሥርዓቱ ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜ ተፈጽሟል የሚል ነው። ይህንን ሐሳብ ከተቀበልን ዘንዳ የታቦቱ ሥርዓት ክርስቶስ ከተገለጠ በኋላ (ለክርስቲያኖች) አያስፈልግም ማለታችን ነው ። የታቦቱ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር በተያያዘ ይደረጉ የነበሩት ሥርዓቶች በሙሉ ማለት ነው ።

የታቦት በክርስቶስ መመሰል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አለ ። የጥምቀት ክብረ በዓል በሚከበርበት ወቅት ታቦቱ ውሃ ወደ ሚገኝበት ሥፍራ (በአዲስ አበባ ወደ ጃንሜዳ በገጠር ደግሞ ወደ ወንዝ) መወሰዱ ክርስቶስ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወርዶ መጠመቁን የሚያመለክት እንደሆነ ይነገራል ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከዚሁ ከታቦተ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ሥርዓቶች ስንመለከት አሁንም ሊመለሱ የማይችሉ ጥያቄዎች ይፈጠራሉ ። ለምሳሌ ታቦቱ በመላእክት ወይም በቅዱሳን አማላጆች መሰየሙ ፍጹም ከብሉይ ኪዳን ወይም ከአይሁድ ባሕል የተወሰደ አይደለም ፥ ለምን ደግሞ በክርስትና ይዘቱ ወይም ትርጓሜ አስፈላጊ እንደሆነ ለመረዳት ያስቸግራል ። ድንገትም በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ፥ የቤተ ክርስቲያን ስያሜ ጋር የተያያዘ ይሆን ? ። በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ለምሳሌ የቤተ ክርስቲያን ስያሜ ሲጀመር በመታሰቢያነት በአንድ ቅዱስ አገልጋይ ወይም በመላእክት ስም ቤተ ክርስቲያኑ ይሰየማል ።

በኋላም እየቆየ የቅዱሱ አጽም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ይቀበርና ቤተ ክርስቲያኑም በዚሁ ቅዱስ ስም መጠራት ተጀመረ ። ከዚህ ጋር በተያያዘ እንደ አቡነ ኀርኀርዮስ እና እንደ ብርሃኑ ኅበና አገላለጽ መንበሩ/ጽላቱ በቅዱሳን ወይም በመለአክት ስም ይሰየማል ማለት ነው ። ይህ ሁኔታ በአይሁድ ባሕል ያልነበረ ነገር ግን በኢትዮጵያውያን የተጨመረ ነው ።

ቀደም ሲል በመጀመሪያው የጽሑፉ ክፍል ስንመለከት

እንደነበረው ታቦቱ ከመሠረቱ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሲሠራ የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ ነበር ። እግዚአብሔርም በዚያ በማስተሰሪያ ክዳኑ ላይ ሕዝቡን ለማነጋገር የሚገለጥበት ሥፍራ እንደነበረም ተመልክተናል ። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር "ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው የሆነውን ክብሩን አየነው" (ዮሐንስ ወንጌል 1፤14) ይላል ሌላ ሥፍራ ደግሞ "...እርሱም (ኢየሱስ ክርስቶስ) የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢአታችን ካነጻ በኃላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ...." (ዕብራውያን 1፤3) ።

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ ከሆነ ዘንዳ የታቦቱ ምሳሌ ነው ማለት ነው ። እግዚአብሔር በዕብራውያን ም1 ቁ1 ላይ እንደምናገኘው በዚህ በመጨረሻ ዘመን የተናገረን በልጁ በኩል ከሆነ ከእንግዲህም የሚያነጋግረን በልጁ በኩል ነው ይኸውም በመጽሐፍ ቅዱስ፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው ማለታችን ነው ። ሌላው በታቦቱ ዙሪያ የሚከናወነው የነበረው ሥርዓት የደም መርጨት ሥርዓት ነበር ። ያም ቢሆን እንደገናም በዕብራውያን መጽሐፍ ላይ እንደምናገኘው ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንዴም ለመጨረሻም ጊዜ የበጎችና የኮርማዎች ደም ሳይሆን የራሱን ቅዱስ እና የከበረ ደም ይዞ ለአንዴም ለመጨረሻም ጊዜ በሰማይ ወዳለው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሥፍራ ወደ እግዚአብሔር አምላካችን ፊት ይዞ ገብቷል ። ከእንግዲህ ወዲህ ለኃጢአት መስዋዕት የሚፈስ ደም የለም በታቦቱ ላይም የሚረጭ ደም አይኖርም ።

እነዚህን ነጥቦች በምንመለከትበት ጊዜ የታቦት ሥርዓቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለፈጸመው ከእንግዲህ ወዲህ በክርስትና ይዘት ውስጥ ሊሠራበት አይችልም ብለን ልንደመድም ያስችለናል ። ስለዚህም ነው በሌሎቹ ማለትም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውጪ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አስፈላጊ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ ጥቅም ላይ ያልዋለው ። አንድ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን አገልጋይ ሲገልጹ " የታቦቱን ምሥጢር የማያውቁ ከአረማዊነት የተመለሱ አብያተ ክርስቲያናት በጠረጴዛ መሰል ለቅዳሴ እንደሚገለገሉ እርግጥ ነው ። በተለይ እንደ ሮማ ካቶሊክ ያሉት እንደእኛም ሆነ እንደሌሎቹ የሠሩ እንደሆነ የተዋረዱ ስለሚመስላቸው ከሌሎች ለመለየት ይህን ያድርጉ እንጂ የታቦትን አስፈላጊነት ጠንቅቀው ያውቁታል ። የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በሚሠራበት የቅዱሳን

አጽም ተፈልጎ ከመንበሩ ይደረግና ከመንበሩ ላይ የጌታ አይነተኛ (ታላቅ) ስእል ያለበት መጎናጸፊያ አድርገው ይቀድሳሉ ባለ ጠረጴዛዎች ሌላም ትርጉም ማለት የምሴተ ሐሙስ ራት ማቅረቢያ የነበረው ነው ይላሉ ይባላል <u>አስፈላጊነቱ ግን የግድ ነው</u> (የታቦት) ብለዋል ::

በእ'ኚህ አገልጋይ አገላለጽ አንደኛ ከአረማውያንነት ወደ ክርስትና የተመለሱ እንደ ሮማ ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት የታቦትን አስፈላጊነት ቢያውቁትም እንደውርደት ስለሚመስላቸው ፥ ከሌሎች ደግሞ ለመለየት ሲሉ ሥርዓቱን አያከብሩም ::

በሁለተኛ ደረጃ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በተመለከተ ደግሞ (ማለትም ሌሎች የአርቶዶክስ እምነት የሚከተሉ ) የታቦት ሥርዓት የሌላቸው ሲሆን በምትኩ የቅዱሳን አጽም ተፈልጎ በመንበሩ ይደረጋል ::

ይህ እንደዚህ ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ሌሎቹም የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ማለትም የአርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሆኑ ማለት ነው ከኢትዮጵያ በስተቀር ሁሉም ከአርማዊነት የተመለሱ ናቸው :: በኢትዮጵያም ቢሆን ከተወሰነው የሕዝብ ክፍል በስተቀረ የተቀረው፥ መንግሥትን ጨምሮ በአብዛኛው አረማውያን እንደነበሩ የታሪክ ዘጋቢዎች ይናገራሉ :: ታዲያ የታቦት ሥርዓት እንደመደንገግ በምትኩ የቅዱሳን አጽም እና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ "ዓይነተኛ" ስእል በማድረግ ይጠቀማሉ :: በመሆኑም ከኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በስተቀረ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የምሥራቁንም የሮማ ካቶሊኩንም እንደዚሁም የፕሮቴስታንቱን ጨምሮ ታቦቱ አስፈላጊነት ያለው ቢሆንም አይጠቀሙበትም ፤ ነገር ግን የታቦቱ አስፈላጊነት የግድ ነው የሚል አስተያየት ነው :: ይህ አመለካከት በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሊኖረው የሚችለው ተቀባይነት የሚያጠራጥር ነው :: ይህ እንደዚህ ከሆነ ታዲያ የታቦት (የግድ) አስፈላጊነቱ እንዴት ይሆን ? በሌላ በኩል ይህ በሙሴ እጅ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የተሠራው የቃል ኪዳኑ ታቦት በኢትዮጵያ የሚገኝ ከሆነ ወደፊት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ እዚያው በአክሱም ከተማ እንደሆነ ይቀራል ? የመጨረሻው ዕድል ፈንታው ምንድን ነው ?

# የቃል ኪዳኑ ታቦት እና የክርስቶስ ምጽአት

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተመራማሪዎችና አዋቂዎች አሁን የምንገኝበት ዘመን የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከመቼውም የበለጠ የተቃረበበት እንደሆነ አበክረው ይናገራሉ ። በአዲስ ኪዳን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 እንደዚሁም በብሉይ ኪዳን በትንቢተ ዳንኤል ላይ የተገለጹት ትንቢቶች እና ምልክቶች በሙሉ በየጊዜው እየተፈጸሙ ስለሆነ የሰው ልጅ ከመቼውም በባለጠ ጥንቃቄ እና ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባው በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚካሄደው ትምህርት ተጧጡፏል ።

ግራንት ጄፈሪ የተሰኙ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ እና በተለይም የክርስቶስ ምጽአት እና የዓለምን መጨረሻ በሚመለከት ብዙ ምርምር ያደረጉ ካናዳዊ Armageddon - Appointment with Destiny በተሰኘው መጽሐፋቸውና እንደዚሁም The Ark of the Covenant and the Red Heifer በሚል ርእስ ባስቀረጹት ትምህርታዊ ቪዲዮ ታቦቱ ስለሚገኝበት ሥፍራና ወደ ፊት ስለሚኖረው ሚና ሰፊ አስተያየት አቅርበዋል ።

ግራንት ጄፍሪ በክብረ ነገሥት ላይ የሠፈረውን በኢትዮጵያውያኖች ዘንድ ለብዙ ዘመን ሲታመንበት የቆየውን ታሪክ ሲዘግቡ ንጉሥ ሰለሞን ከንግሥት ሳባ ምኒሊክን ከወለደ በኋላና ምኒልክም አድጎ ወደ አገሩ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ በፈለገ ጊዜ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም እየመጣ በቤተ መቅደስ ውስጥ ለማምለክ ስለሚቸግረውና መንገዱም ሩቅ ስለሆነ ይዞት የሚሄደውን ታቦት ቅጂ አሠርቶለት እንደነበር ዘግበዋል ። ነገር ግን ምኒልክ የአባቱን ከእግዚአብሔር መንገድ መራቅ ስለተመለከተ እና ጣኦቶችን ማምለኩ እያሳሰበው በመምጣቱ ቅጂውን ሳይሆን ዋነኛውን ታቦት ሰርቆ እንደወሰደ ይናገራሉ ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግመ ምጽአት አስመልክቶ ሊፈጸሙ ከሚገባቸው በርካታ ትንቢቶች መካከል ዋነኛው የእሥራኤል ቤተ መቅደስ ለሦስተኛ ጊዜ መሠራት እንደሆነ ገልጸዋል ። እንደሚታወሰው ሁሉ የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ በንጉሥ ሰለሞን ነበር የተሠራው ። ይህ ቤተ መቅደስ በባቢሎናውያን በተወረረ ጊዜ ፈጽሞ እንደፈረሰ እናውቃለን ።

ሁለተኛው ቤተ መቅደስ በ 516 ዓዓ በነዘሩባቤል፥ ዕዝራና ነህመያ ዘመን እንደተሠራ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመመልከት እንችላለን።

ይህ ቤተ መቅደስ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር እየተዘዋወረ በተመላለሰበት ዘመን ሥራው ተጠናቆ ነበር። በአንድ ሥፍራ ላይ እንዲያውም ጌታ ኢየሱስ ለአይሁዳውያን ይህንን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀን እንደገና አስነሳዋለሁ ብሎ ሲናገራቸው ፥ እነርሱ ስለ ሰውነቱ መናገሩን ሳያስተውሉ ቀርተው እንዴት ያን ያህል ዘመን የፈጀን ሕንጻ በሦስት ቀን አስነሳዋለሁ ይላል ብለው እንደመለሱ ትዝ ይለናል። ይህ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ በ70 ዓም በሮም መንግሥት ወታደሮች እንደተቃጠለ ከታሪክ ማኅደር ለመረዳት ይቻላል።

እንደ ግራንት ጄፍሪ አገላለጽ የዓለም መጨረሻ ከመድረሱ በፊት ቤተ መቅደሱ ለሦስተኛ ጊዜ ይሠራል ። ይህም ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዋነኛ ምልክት ይሆናል ባይ ናቸው ። ለዚህም ማስረጃ የሚያቀርቡት ከብሉይ ኪዳን ከትንቢተ ዳንኤል በመጥቀስ ነው ። "ዓመፃን ይጨርስ ፥ ኃጢአትንም ይፈጽም ፥ በደልንም ያስተሰርይ ፥ የዘላለምን ጽድቅ ያገባ ፥ ራእይንና ትንቢትን ያትም፥ ቅዱሰ ቅዱሳኑንም ይቀባ ዘንድ በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቆጥሮአል ። ስለዚህ እወቅ አስተውልም ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሲሕ ድረስ ሰባት ሱባኤና ስድሳ ሁለት ሱባኤ ይሆናል አርስዋም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች ። ከስድሳ ሁለትም ሱባኤ በኋላ መሲሕ ይገደላል ፤ በእርሱም ዘንድ ማንም የለም የሚመጣው አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ ፍፃሜውም በጎርፍ ይሆናል ፥ እስከ መጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል ጥፋትም ተቆጥሮአል ። እርሱም ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባኤ ያደርጋል ፤ በሱባኤውም አኩሌታ <u>መሥዋዕቱንና</u> ቁርባኑን ያስቀራል በርኩሰትም ጫፍ ላይ አጥፊው ይመጣል እስከ ተቆጠረውም ፍፃሜ ድረስ መቅሰፍት በአጥፊው ላይ ይፈስሳል" ። (ዳንኤል 9፤24-27)

ግራንት ጄፍሪ በተለይም በቁጥር 27 ላይ ከላይ የተሰመረባቸውን ክፍል አስመልክተው ይህ ፀረ ክርስቶስ (የክርስቶስ ተቃዋሚ) በሚያደርገው የእርቅ ድርድር አጋማሽ ላይ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚካሄደውን የመስዋዕትና የቁርባን ሥርዓት ያስቀራል ስለሚል በአሁኑ ጊዜ (ከ70 ዓም በኋላ) ይህን የመሰለ መስዋዕትና ቁርባን የሚቀርብ ስለሌለ ይህ ጸረ ክርስቶስ ከመገለጡ

በፊትና ከእሥራኤል ጋር የአንድ ሱባኤ ወይም የሰባት ዓምት የሰላም ድርድር ከማድረጉ በፊት የመስዋዕትና የቁርባኑ ሥርዓት እንደገና በአይሁዶች ዘንድ መመሥረት አለበት ፤ ሥርዓቱን ለመመሥረት ደግሞ ቤተ መቅደሱ እንደገና መሠራት ይኖርበታል ፤ ቀደም ሲል ደጋግመን እንደተናገርነው ደግሞ የቤተ መቅደሱ መሠራት የሚያስፈልገው ታቦቱን በውስጡ ለማኖር ነው ። እነዚህ ሁሉ የተያያዙ ናቸው ።

ይህንን አስተያየት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቶቹ ስለ መጨረሻው ዘመን ምልክት እንዲሰጣቸው በጠየቁት ጊዜ በሰጣቸው መልስ ላይም እንደሚገኝ በመግለጽ ግራንት ጄፍሪ ማስረጃቸውን ያጠናክራሉ ። “እንግዲህ በነቢዩ ዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት <u>በተቀደሰችው ሥፍራ</u> ቆሞ ስታዩ ፥ አንባቢው ያስተውል በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ በሰገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ፥ በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ” ። (ማቴዎስ 24፤15-17) ። በተቀደሰችው ሥፍራ የተሰኘው ቤተ መቅደሱን/ቅድስተ ቅዱሳኑን ለማመልከት ነው ።

እንደገናም ግራንት ጄፍሪ ይህንኑ ሐሳብ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው በሁለተኛው መልዕክቱ እንዳሰፈረው ይገልጻሉ ። “ማንም በማናቸውም መንገድ

እንደተናገሩ ጠቅሰዋል ። ታዲያ በዚህ በሦስተኛው ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚቀመጠው ታቦት ከየት ነው የሚመጣው ?

በኚሁ ካናዳዊ ጸሐፊ መሠረት ታቦቱ አሁን ከሚገኝበት ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅድሱ ውስጥ ሊቀመጥ ይመጣል ። ለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማስረጃ እናገኛለን ይላሉ ። የመጀመሪያው ማስረጃቸው በትንቢተ ኢሳያስ ምዕራፍ 18 ላይ የሚገኘውን በመጥቀስ ያቀርባሉ ። "በኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ላለች ክንፍ ያላቸው መርከቦች ላሉባት መልእክተኞችን በባሕር ላይ ለምትልክ ምድር ወዮላት! እናንተ ፈጣኖች መልእክተኞች ሆይ ወደ ረጅምና ወደ ለስላሳ ሕዝብ ከመጀመሪያው አስደንጋጭ ወደ ሆነ ወገን ወደ ሚሰፍርና ወደሚረገጥ ወንዞችም ምድራቸውን ወደሚከፍሉት ሕዝብ ሂዱ ። በዓለም የምትኖሩ ሁሉና በምድር የምትቀመጡ ሆይ ምልክት በተራሮች ላይ በተነሣ ጊዜ እዩ መለከትም በተነፋ ጊዜ ስሙ ። ......በዚያን ዘመን ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ከረጅምና ከለስላሳ ሕዝብ ከመጀመሪያው አስደንጋጭ ከሆነ ወገን ከሚሰፍርና ከሚረግጥ ወንዞችም ምድራቸውን ከሚከፍሉት ሕዝብ ዘንድ <u>እጅ መንሻ</u> የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ስም ወደሚገኝበት ስፍራ ወደ ጽዮን ተራራ ይቀርባል" ። (ኢሳያስ 18 ፤ 3 ፥4 እና 7) ።

በዚህ ምንባብ መሠረት ግራንት ጄፍሪ የሚቀርበው እጅ መንሻ ወይም መስዋዕት ታቦቱ ነው ባይ ናቸው ። በዕብራይስጥ ቋንቋ ለእጅ መንሻው የተጠቀሙበት ቃል "ኔስ" የሚል ሲሆን ይህ በብዙ ሥፍራ በተለያየ ቃል የተተረጎመ ከመሆኑም ሌላ ትርጉሙም እንደ ስንደቅ ዓላማ (መለያ) ሊጠቅም የሚችል በጣም ጠቃሚ የሆነ የክብር ዕቃ ሊሆን እንደሚችል ያስባሉ ። ስለዚህም ይህ "ኔስ" የተሰኘ ቃል የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚያመለክት ሊሆን ስለሚችል በዚህ ሥፍራ ለሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚቀርበው እጅ መንሻ ይኸው ታቦት ሊሆን ይችላል ብለው ያምናሉ ።

ሌላው ግራንት ጄፈሪ የሚጠቅሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ትንቢተ ሶፎኒያስ ነው ። ምዕራፍ 3 ቁጥር 9-10 እንደዚህ ይላል ። " በዚያን ጊዜም አሕዛብ ሁሉ አንድ ሆነው እግዚአብሔርን ያገለግሉት ዘንድ ስሙን እንዲጠሩ ንጹሑን ልሳን አምልስላቸዋለሁ ። ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል" ። በዚህ ሥፍራ ላይ ሁለት ትንቢቶችን እንመለከታለን ። የመጀመሪያው የዕብራይስጥ ቋንቋ እንደገና በሕዝቡ መካከል የመመሥረቱ ጉዳይ ነው ። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜ አንስቶ ዕብራይስጥ እየሞተ የሄደ ቋንቋ ነበር ። በጸሐፎችና በካህናት ዘንድ

ብቻ የሚነገር ቋንቋ ነበር ። በአብዛኛው ሕዝብ የሚነገረው ቋንቋ ግሪክ ሲሆን ልክ እንደዛሬው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ነበር ። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ ቋንቋ እንደገና ተመሥርቶ እናገኘዋለን እግዚአብሔር ደግሞ ይህንን ቋንቋ ንጹሕ ቋንቋ በማለት ይጠራዋል። በትንቢቱ የተጠቀሰው ሁለተኛው ሐሳብ ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚመጠውን ቁርባን ወይም ሥርዓት የተመለከተ ሲሆን ግራንት ጀፍሪ ይህ መስዋዕት/ ቁርባን የቃል ኪዳኑ ታቦት ይሆናል ብለው ይገምታሉ ።

በሦስተኛ እና በመጨረሻ የጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ትንቢተ ኤርሚያስን ነው ። በምዕራፍ 3 ቁጥር 16-17 ላይ ያለው ቃል እንደዚህ ይላል "በበዛችሁም ጊዜ በምድርም ላይ በረባችሁ ጊዜ ይላል እግዚአብሔር በዚያን ዘመን - የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ብለው ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሩም ልብ አያደርጉትም አያስቡትም አይሹትምም ከእንግዲህ ወዲህ አይደረግም ። በዚያን ዘመን ኢየሩሳሌምን የእግዚአብሔር ዙፋን ብለው ይጠሩአታል አሕዛብም ሁሉ ወደ እርስዋ ይሰበሰባሉ ከእንግዲህም ወዲህ ክፉውን እልከኛ ልባቸውን ተከትለው አይሄዱም" ። በዚህ ምንባብ መሠረት ይላሉ ግራንተ ጀፍሪ ኤርሚያስ እየተነበየ ያለው ከአርማጌዶን ጦርነት በኋላ እሥራኤል በመሲሑ ግዛት እያለች የሚሆነውን ነው ። ስለሆነም በዚያን ጊዜ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት አያወሩም አይፈልጉትም ፥ አይነበኙትም ። ለምን ? በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ እንደመሲሑና እንደ ንጉሥ ሊመለክ በመካከላቸው ስለሚገኝ ነው በማለት ያስረዳሉ ። ይህ እንዲህ ከሆነ ታዲያ ፥ ትንቢቱ ትርጉም ሊሰጥ የሚችለው ታቦቱ አሁን ከሚገኝበት ሥፍራ ወደ ቤተ መቅደሱ ከተመለሰ በኋላ ብቻ ነው ።

ለማጠቃለል ታዲያ ታቦቱ አሁን በኢትዮጵያ ይገኛል ። ድንገትም እግዚአብሔር የዘመን መጨረሻ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት እስኪቃረብ ድረስ ተጠብቆ እንዲቆይ በኢትዮጵያ ታቦቱ እንዲኖር አድርጓል ። እርሱ ያቀደው ጊዜ ሲደርስ የእሥራኤል ቤተ መቅደስ ለሦስተኛ ጊዜ እንደገና ይሠራል ፤ ታቦቱ ከሚገኝበት ሥፍራ ወደ ኢየሩሳሌም እንደ መስዋዕት ሆኖ ይቀርባል ፤ ጸረ ክርስቶስ የአመጽ ሰው ከእስራኤል ጋር የሰባት ዓመት ድርድር ያደርጋል ፤ በድርድሩ አኩሌታ ላይ እኔ እግዚአብሔር ነኝ በማለት ቃል ኪዳኑን አፍርሶ ቤተ መቅደሱን ይደፍራል ፤ በዚያም የሚከናወነውን የመስዋዕትና የቁርባን ሥርዓት ይከለክላል ከዚያም የጌታ መምጫ ይሆናል ባይ ናቸው።

የቃል ኪዳኑ ታቦት በኢትዮጵያ መገኘት አስመልክቶ ክርስቲያናዊ ይዘቱን በተመለከተ ግን ግራንት ጀፍሪ ምንም ዓይነት

አስተያየት በመጽሐፋቸውም ሆነ በቪዲዮ ላይ አልሰጡም ። የታቦቱ በኢትዮጵያ መገኘት ከላይ የተመለከትነውን ትንቢት እንስኪፈጸም የሚጠብቅ ከሆነ ዛሬ ክርስቲያናዊ ይዘት ተሰጥቶት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ መዋሉ እንዴት እንደሚመለከቱት ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ሲጠየቁ የሰጡት መልስ ባህላዊ ይዘት እንደዳለው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ ነው።

ይህንን ጽሑፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት ግራንት ጄፍሪን ካነጋገርኩኝና በቅርቡም በገበያ ላይ ያዋሉትን የመጽሐፋቸውን እትም ከተመለከትኩኝ በኃላ ለማመን አስቸጋሪ የሆነ መረጃ አገኘሁኝ ። ይኸውም ታቦቱ በአሁኑ ጊዜ በእሥራኤላውያን ዘንድ እንደሚገኝ የሚያመለክት ነው ።

እንደ ግራንት ጄፍሪ አገላለጽ ታቦቱ በእሥራኤላውያን ዘንድ የደርግ መንግሥት ሊወድቅ በነበረበት ዋዜማ በኢትዮጵያ የሚገኙ ፈላሻዎች ወደ እሥራኤል እንዲሄዱ በተፈቀደበት ጊዜ ታቦቱም ከእነርሱ ጋር በመንግሥት ፈቃድ በሚስጥር ተወስዷል ።

ግራንት ጄፍሪ መረጃቸውን ያገኙት ከሚያምኗቸውና በዚሁ ጉዳይ በቅርብ ግንኙነት ከነበራቸው አንድ ኢትዮጵያዊ የቀድሞ ባለሥልጣን ፥ አንድ እሥራኤላዊ ባለሥላጣንና አንድ የካናዳ ዲፕሎማትና የፓርላማ አባል ናቸው ። የሰነዘሩት መረጃ ይህን ይመስላል።

ሦስቱም ግለሰቦች የሰጡት መረጃ በጦርነቱ መጨረሻ አካባቢ በእሥራኤልና በኢትዮጵያ መሪዎች መካከል ስለታቦቱ ወደ እሥራኤል መመለስ ድርድር ይደረግ እንደነበር ፥ የኢትዮጵያ መሪዎች ይህንን ለመፍቀድ ብዙ ሚሊዮን ዶላር እንደጠየቁ ፥ ይህ ገንዘብ እንደተዋጣ እና በሁለት ሻንጣ ሙሉ የውሸት ገንዘብ ተደርጎ ለባለሥልጣኖቹ እንደተሰጠ ፤ ባለሥልጣኖቹም ወደ ስዊስ ይዘው እንደጠፉ ፤ በሌላ በኩል ግን እውነተኛውን ገንዘብ የአገሪቱን ከተማ ለተቆጣጠሩት የኢህአዴግ መንግሥት እንደተሰጠ ፤ ከዚያም የእሥራኤል የጦር አውሮፕላን ወደ ጎንደር በሚስጥር በሮ በእሥራኤል ወታደሮች አማካኝነት በድብቅ ታቦቱን ከነበረበት ከአክሱም ጽዮን ወደ ኢየሩሳሌም እንደወሰዱት ፤ አሁንም በሚስጥራዊ ሥፍራ እንደተቀመጠ ጊዜውም ደረሰ የመቅደሱ እንደገና መገንባት ሲጠናቀቅ በሥፍራው ላይ ይቀመጣል የሚል ነው።

ይህንን መረጃ ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ነው ። ሆኖም ግን ግራንት ጄፍሪ መረጃውን ያካፈሏቸውን ግለሰቦች እንደሚያምኗቸው ዘግበዋል። ምን ያህል እውነት ነው ወደፊት ይታያል !

# የቃል ኪዳኑ ታቦት ክርስቲያናዊ ይዘት

የቃል ኪዳኑን ታቦት ጨምሮ በማደሪያው ድንኳን ይገኙ የነበሩትን የአምልኮት ዕቃዎችና ሥርዓቶች በአዲስ ኪዳን መነጽር በምንመለከትበት ጊዜ የሚያሳዩት ክርስቲያናዊ ይዘት ቀደም ሲል ከተመለከትነው ፍጹም የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን ::

በአዲስ ኪዳን የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦትና በዙሪያው ስለሚደረገው ሥርዓተ አምልኮ ሲጽፍ እንደዚህ ይላል ::

"ፊተኛዪቱ ደግሞ የአገልግሎት ሥርዓት የዚህ ዓለም የሆነው መቅደስ ነበራት :: የመጀመሪያይቱ ድንኳን ተዘጋጅታ ነበርና በእርሰዋም ቅድስት በምትባለው ውስጥ መቅረዙና ጠረጴዛው የመሥዋዕቱም ኅብስት ነበረባት :: ከሁለተኛው መጋረጃ ወዲያ ቅድስት ቅዱሳን የምትባለው ድንኳን ነበረች :: በዚያም ውስጥ የተለበጠች የኪዳን ታቦት በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ በላይዋም ማስተስሪያውን የሚጋርዱ የክብር ኪሩቤል ነበሩ :: ስለ እነዚህም ስለ እያንዳንዳቸው ልናገር አሁን አልችልም ..... ፊተኛዪቱ ድንኳን በዚህ ገና ቆማ ሳለች ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል :: ይህም ለአሁኑ ጊዜ ምሳሌ ነው :: እንደዚህም መባና መስዋዕት ይቀርባሉ :: እነዚህም እስከ መታደስ ዘመን ድረስ የተደረጉ ስለ ምግብና ስለ መጠጥም ስለ ልዩ ልዩ መታጠብም የሚሆኑ የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ናቸውና የሚያመልከውን በሕሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም :: (ዕብራውያን 9፤1-10)

እንደገናም በምዕራፍ 10፤ ቁጥር 1 ላይ " ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና" ይላል :: የዕብራውያን ጸሐፊ መልዕክቱን ያዘጋጀው ለአይሁዳውያን ክርስቲያኖች እንደሆነ በአጠቃላይ መልዕክቱን በምናነብበት ጊዜ ለመረዳት ይቻላል :: ዓላማውም (በተለይ በምዕራፍ 9 ÷ 10) በብሉይ ኪዳን የነበሩት ሥርዓቶች ማለትም በድንኳኑ ውስጥ ይደረጉ የነበሩት ሥርዓቶች ምሳሌያዊ ይዘት ያላቸውና እውነተኛ አካለቸው የተገለጠው በክርስቶስ ማንነተና አገልግሎት እንደሆነ ለማስረዳት ነበር ::

ይህንን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኘውን ክርሲተያናዊ ይዘት ሰፋ ባለ መልኩ በርእሱ ላይ ሀሳባቸውን ከሰነዘሩት በርካታ ግለሰቦች መካከል ሚስተር ዴቪድ ሌቪ የተሰኙ አሜሪካዊና ዶ/ር ዓለሙ ቢፍቱ የተሰኙ ኢትዮጵያዊ ካበረከቱት ሀሳቦች በመጥቀስ ከዚህ በታች እንመልከት።

በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረትና በሙሴ አማካኝነት እሥራኤላውያን አምላካቸውን የሚያመልኩበት ሥርዓት ፥ የማደሪያው ድንኳን እና በውስጡ የሚገኙትን የአምልኮት ዕቃዎች ፥ አሠራራቸው ፥ ቅርጻቸው ፥ የሚገኙበት ሥፍራን በተመለከተ ቀደም ሲል በጽሑፉ መግቢያ ስለተገለጸ እንደገና በዚህ ሥፍራ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም ። ነገር ግን እያንዳንዱ ሥርዓትና የአምልኮት ዕቃ በምን ዓይነት ሁኔታ የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ እንመለከታለን ።

1ኛ) የናስ መሠውያ:- በመጀመሪያ ደረጃ መሠውያው ከየተሠራቀበትን ስንመለከት ከግራር እንጨት ሲሆን በናስም የተለበጠ ነበር ። የግራር እንጨቱ የተመረጠበት ምክንያት ጠንካራ፥ የማይበሰብስና የማይበላሽ እንጨት ስለሆነ ነው ። ይህም ደግሞ የክርስቶስ ምሳሌ ነው ። የግራር እንጨት መበስበስን የማያይ የክርስቶስን ሥጋ የሚያመለክት ነው ። የግራሩ እንሠት በናስ መለበጡ ደግሞ ናስ የእግዚአብሔር ፍርድን የሚያመለክት ነው ። እንደ ዶ/ር ዓለሙ አገላለጽ "የግራር እንጨት የሚመረጥበት ነገር ቢኖር በፍጹም ስለማይበሰብስ ነው ። የሳይንስ ሊቃውንት ጠንካራ እንጨት በመዳብ ከተለበጠ እሳት ይከላከላል ይላሉ ።

የክርስቶስ ሥጋ በእግዚአብሔር ቁጣ ተቃጥሎ ሳያልቅ የመሠውያው ምሳሌ በሆነው በቀራንዮ መስቀል ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ተሸከሞ እንዴት እንደቻለው ስናስተውል በጣም አስደናቂ ሆኖ እናገኘዋለን ። ሙሴ አይቷት የነበረችው ቁጥቋጦ እሳት ሲነድባት እርሷ ግን እንዳልተቃጠለች ሁሉ ክርቶስም በእግዚአብሔር ቁጣ ሳይጠፋ ፍርዳችንን ተሸከመ " ።

ይህ የናስ መሠውያ አገልግሎቱ መስዋዕት የሚቀርብበት ሥፍራ ነበር ። ይህ ደግሞ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን እንደ ሚታረድ በግ እራሱን መስዋዕት አድርጎ ማቅረቡን ያመለክታል ። በዘሌዋውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 9 ላይ "ካህኑም ሁሉን የሚቃጠል መሥዋዕት የእሳት ቁርባን አድርጎ በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን በመሠውያው ላይ ያቃጥለዋል" ይላል ። ይህም በአዲስ ኪዳን በኤፌሶን ምዕራፍ 5 ፥ 2 ላይ ጳውሎስ ስለክርስቶስ ወደ ጻፈው

ያመለክተናል ። "ክርስቶስም ደግሞ እንድ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለእናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ" ።

2ኛ/ የመታጠቢያ ሳህን:- ይህ ካህናቶች ብቻ የሚጠቀሙበት ሲሆን ከአግልግሎተ በፊትም ሆነ በአገልግሎት መካከል እንደ አስፈላጊነቱ ለመታጠብ የሚጠቀሙበት ዕቃ ነው ። ዶ/ር ዓለሙ ስለመታጠቢያው ሳህን ሲያበራሩ እንዲህ ይላሉ "ናሱ የእግዚአብሔር ፍርድ ምሳሌ ነው ። ውኃውም የእግዚአብሔር ቃል ምሳሌ ነው ። የእግዚአብሔር ቃል ዕድፍን የሚያነፃ ፍጹም ውኃን ይመስላል" ።

3ኛ/ የወርቅ መቅረዝ:- ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የምንመለከታቸው ከአደባበዩ ወደ ቅድስት ሥፍራ ስንገባ የምናገኛቸውን የአምልኮት ዕቃዎችን ነው ። ከነዚህም በመጀመሪያ የወርቅ መቅረዙን እንመልከት።

ይህ መቅረዝ የተሠራው አንድ ወጥ ከሆነ ወርቅ ሲሆን ይህም ደግሞ የክርስቶስን ፍጹም መለኮት የሚያሳይ ነው ። ይህ የወርቅ መቅረዝ በቅድስት ሥፍራ ያለማቋረጥ ብርሃን የሚሰጥ ሲሆን የሚንከባከቡትም ካህናቶቹ ናቸው ። ብርሃን መስጠቱ የክርስቶስ ምሳሌ ነው ። ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነው ። "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም" - (ዮሐንስ 8÷12) ። እንደገናም ሐዋርያው ዮሐንስ በአንደኛ መልዕክቱ ምዕራፍ 1 ቁጥረ 5 ላይ "እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ከቶ የለም" በማለት አረጋግጧል ።

መቅረዙ ብርሃን ለመስጠት ዘይት ማግኘት አለበት ። ለዚህም የሚጠቀሙበት የወይራ ዘይት ነበር ። ዘይት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው ። ይህ ዘይት በቅድስት ውስጥ የሚያበራ ብርሃን እንደሚሰጥ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም በሕይወታችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ብርሃን እንደሚያበራ ያመለክታል ።

4ኛ/ የኅብስቱ ገበታ:- ይህ የኅብስት ገበታ የሚሠራው ከግራር እንጨት ሲሆን በንጹሕ ወርቅም ይለበጣል ። ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የግራር እንጨቱ የክርስቶስን ማንነት የሚያሳይ ሲሆን በወርቅ መለበጡ ደግሞ የክርስቶስን ሰውና አምላክነት የሚያሳይ ነው ። የገበታው ዋናው ሥራ ኅብስቱን ማስቀመጫ ነው ። ይህ ኅብስት የተለያየ መጠሪያ ያለው ሲሆን በአንድ ሥፍራ የገጽ ኅብስት ተብሎ ተጠቅሷል ። ይህም ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት (ገጽ) ፊት እንዲቀመጥ በመደረጉ ነው ።

ይህ ኅብስት የክርስቶስ ምሳሌ ነው ። ክርሰቶስ የሕይወት

እንጀራ ነው ። "የሕይውት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም" (ዮሐንስ 6፥35) ። እንደገናም ይህ ኅብስት የሚሠራው እርሾ ሳይገባበት ነው ። ይህም ደግሞ ክርስቶስ ያለ ኃጢአት የተገለጸው የሕይወት እንጀራ እንደሆነ የሚያሳይ ነው ።

5ኛ/ <u>የዕጣን መሰውያ</u>፦ ይህ የዕጣን መሠውያ የተሠራው ከግራር እንጨት ሆኖ የተለበጠው ደግሞ በወርቅ ነበር ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው መሠውያው ከግራር ተሠርቶ በወርቅ መለበጡ የክርስቶስን ሰውነትና አምላክነት የሚያመለክት ነው ። በዕጣኑ መሠውያ የሚነደው ዕጣን ጣፋጭ የሆነ ሽታ ይፈጥራል ። ይህ ደግሞ የክርቶስ መስዋዕት በእግዚአብሔር ፊት አርኪ እንደሆነ ያመለክታል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ መሠውያ የጸሎት ምሳሌ ነው ። በዚህ መሠውያ ላይ ደግሞ አራት ቀንዶች ነበሩ ። ቀደም ሲል እንደተመለከተው ቀንድ የኃይል ምሳሌ ነው ፥ በመሆኑም የጸሎት ኃይልን የሚያመለክት ይሆናል ማለት ነው ። ይህንን በተመለከተ ዶ/ር ዓለሙ ሲጽፉ "ለዕጣኑ መሠውያ የሚያስፈልገው እሳት የሚሰወደው ከናሱ መሠውያ ላይ ብቻ ነው ። እሳቱ ከሌላ ቦታ የመጣ ከሆነ ግን በእግዚአብሔር ቁጣ መቅሰፍትን ያስከትል ነበር .... የክርስቲያን ጸሎት ኃይል የሚኖረው በቀራንዮ መስቀል መሥዋዕት በሆነልን በክርስቶስ ስም ሲጸለይ ብቻ ነው ። ያለ ክርስቶስ ጸሎት ኃይል የለውም ። ስለዚህ በመስቀል ላይ መሥዋዕት በመሆን እራሱን ለኛ የሰጠው ጌታ 'እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና አብም ስለወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ' ይላል። የክርስቲያን ጸሎት የኃይሉ ምሥጢር ከመስቀሉ ነው ።"

6ኛ/ <u>መጋረጃ</u>፦ አሁን ደግሞ ከቅድስት ሥፍራ ወድ ቅድስተ ቅዱሳኑ ለመግባት እያመራን እንገኛለን ። የቅድስቱን እና የቅድስተ ቅዱሳኑን የሚለየው ከተለያዩ ቀለሞች የተሠራው መጋረጃ መበር ። ይህ መጋረጃ ለጌጥ ሳይሆን አገልግሎቱ በቅድስቱና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል እንድ መለያ እንዲሆን ነበር ። በዚህም መሠረት ኃጢአተኛውን ከቅዱሱ እግዚአብሔር ለመለየት የተደረገ ነው ።

ይህ መጋረጃ የክርስቶስ ምሳሌ ነው ። እንደምናስታውሰው ሁሉ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ኃጢአት ራሱን አሳልፎ በመስቀል ላይ በሰጠ ጊዜ ይህ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደደ ። ማቴዎስ 27፥ ከቁጥር 45 ጀምሮ ታሪኩን ስንመለከት " ከስድት ስዓትም ጀምሮ አስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ ። በዘጠኝ ሰዓትም

ኢየሱስ - ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ ጮኸ ...... እነሆም የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ ....” ይህ የመጋረጃው መቀደድ የሚያመለክተው በሰው እና እግዚአብሔር መካከል ተዘግቶ የነበረው መንገድ በክርስቶስ የስቅለት ሞት መከፈቱን ነው ። የመጋረጃው መቀደድ የክርስቶስ ሥጋ መቆረስ ምሳሌ ሲሆን በሞቱ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር እርቅን እንዳገኘ ያመለክታል ። ይህንኑ ሐሳብ ዕብራውያን 10፥19-20 እንዲህ በማለት ያብራራል “እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን በእግዚአብሔር ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና....” ።

7ኛ/ <u>የቃል ኪዳኑ ታቦት</u>፡- በጽሑፉ በሰፊው ለመመልከት እንደተመከረው ሁሉ የታቦት አሠራር አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ከግራር እንጨት ተሠርቶ በንጹሕ ወርቅ የተለበጠ ነበር ። በውስጡም መና ያለበት መሶብ ፥ የአሮን በትር እና ሁለቱ የኪዳኑ ጽላቶች ነበሩ ። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ሁሉ የግራሩ በወርቅ መለበጥ በሰው ምሳሌ የተገለጠው የኢየሱስን አምላክነት የሚያሳይ እንደሆነ ተመልክተናል ። እንደ ዶ/ር ዓለሙ አገላለጽ “ የወርቁ በውጭና በውስጥ መለበጥ የሚያሳየው ክርስቶስ ከዚህ በፊት አምላክ እንደሆነ ለወደፊትም ለዘላለም በአምላክነቱ እንደሚኖር ነው ። በመካከል ያለው ግራር ደግሞ ....ሥጋ ለብሶ የተመሳለሰበትን ሰውነቱን ያሳያል ” ይላሉ ። የዮሐንስም ወንጌል ይህንኑ ሐሳብ ይደግፋል “ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ .... ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጁም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን።” (ዮሐንስ 1፥1 እና 14) ታቦቱ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ መቀመጡ ፥ ታቦቱ የእግዚአብሔር ክብር ወይም መገኘት ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን አምላክ በሰው መካከል መገኘቱን የሚያመለክት ነበር ። በተመሳሳይ ሁኔታም ክርስቶስ አምላክ ሆኖ ሳለ በፍጥረቱ መካከል መመሳለሱን የታቦቱ ተምሳሌነት ያሳየናል ።
እንደገናም ዶ/ር ዓለሙ ይህንን በተመለከተ ሲያብራሩ “ታቦቱ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ነበር ፤ ሲሄዱም በአንድ በተወሰነ ቦታ ሲሰፍሩ አብሮአቸው ነበር ። ታቦቱ ከሌለ ክብር አልነበረም ክብራቸው እርሱና በእርሱ ነበር ። ክርስቶስ ዛሬ በቤተ

ክርስቲያኑ መካከል ነው ። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካልና ሙላት ስለሆነች ያለ እርሱ ለመኖር አትችልም ። ስለዚህም ነው 'እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ' በማለት ታላቅ መሠረት የጣለላት ።"

ከዚህ በተጨማሪ የቃል ኪዳኑ ታቦት ብቻ ሳይሆን በውስጡ የነበሩትም ነገሮች የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆኑ ለመመልከት ይቻላል። በመጀመሪያ ደረጃ በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ የነበረው በመሶብ ውስጥ የሚቀመጠው መና ነበር ። ይህ መና እሥራኤላውያን ከግብጽ ምድር ወጥተው በምድረ በዳ በተጓዙበት ጊዜ እግዚአብሔር ከሰማይ እያወረደ የመገባቸው ምግብ ነበር ። ይህ መና በተለያየ ሁኔታ የክርስቶስ ምሳሌ ይሆናል ። በመጀመሪያ ከዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ፥ 31 ጀምሮ ስናነብ በምናገኘው መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀመዛሙርቱ እና ይከተሉት ከነበረው ሕዝብ ሙሴ ለእሥራኤላውያን በምድረ በዳ መናን በማዝነብ ምልክት እንዳሳያቸው ሁሉ እርሱም ምልክት እንዲያሳያቸው ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ " እውነት እውነት እላችኋለሁ እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም ፤ የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው ። ስለዚህም - ጌታ ሆይ ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት ። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው - የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ......(ቁጥር 48 ጀምሮ) የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ። አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉም ሞቱም ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው ። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል እኔም ስለዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው " ያለውን ሲሆን በዚህም ክፍል መሠረት ክርስቶስ ከሰማይ የወረደው መና እንደሆነ እንመለከታለን ።

እንደዚሁም ይህ የመናው ተምሳሌነት

ሀ) በምድረ በዳ የዘነበው መና ለሁሉም እኩል እና በነፃ የተሰጠ ነበር ። ክርስቶስም ለሁሉም የሚሆን አዳኝ ሲሆን በነፃ በእግዚብሔር ጸጋ የተሰጠ ስጦታ እንደሆነ ከዮሐንስ ወንጌል 3፥ 16 እና 6፥51 ለማየት ይቻላል ።

ለ) መናው መልኩ ነጭ ነበር ፥ ይህም የክርስቶስን ጽድቅ ያመለክታል ።

ሐ) የመናው አወራረድ እንደ ውርጭ በየዕለቱ የሚወርድ ነበር ። ይህም የክርስቶስን ሁልጊዜ አዲስነት ያመለክታል ።

ሌላው በቃል ኪዳን ታቦት ውስጥ የሚቀመጠው የአበበችው

የአሮን በትር ነበረች ። በኦሪት ዘኁልቁ ምዕራፍ 16 እና 17 ላይ እንደምንመለከተው ቆሬ ፥ ዳታን ፥ አቤሮንና አን የተባሉ እሥራኤላውያን በሙሴና በአሮን ተነሥተው በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር የተነሳውን ማጉረምረም ለማቆም የመረጠው አገልጋይ ማን እንደሆነ ለማሳየት ከ12 ነገዶች አንድ አንድ በትር እንዲቀርብና በሌዊ ነገድ በትር ላይ የአሮን ስም እንዲፃፍበት አዟቸው ፥ የምታቆጠቁጠው በትር የእግዚአብሔር ምርጫ እንደሚሆን ከገለጸላቸው በኃላ በበነጋው የአሮን በትር አቆጥቁጣና ለምልማ እንደዚሁም አብባ የበሰለ ለውዝም እፍርታ እንደተገኘች እናያለን ።

የዚህች ያቆጠቆጠች በትር የምታመለክተው የክርስቶስን ትንሣኤ ነው ። ክርስቶስ ሞትን አሸንፎ በሦስተኛው ዕለት መነሳቱን ያመለክታል ። አብባ ፍሬ ማፍራቷ ደግሞ የክርስቶስ ትንሣኤ በክርስቲያኖች ዘንድ ፍሬ የሚያስገኝ ኃይል እንደሆነ ይገልጻል ።

በመጨረሻም በቃል ኪዳን ታቦት ውስጥ የምናገኘው አሥርቱ ቃላት የተጻፉባቸውን ጽላቶች ይሆናል ። የእነዚህ ተምሳሌነት በዶ/ር ዓለሙ አገኅለጽ " 1ኛ/ ሕግ የተጻፈ ቃል ሲሆን ክርስቶስ ለዘላለም የሚኖር ሕያው ቃል መሆኑን ... 2ኛ/ የእግዚአብሔር ሕግ በፍጹም የማያልፍ ዘላለማዊ መሆኑን ያሳያል (እውነት እላችኃለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም)..3ኛ/ ታቦቱ የክርስቶስ ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን የእግዚአብሔር ሕግ ፍፃሜ ያገኘው በክርስቶስ ውስጥ መሆኑን ያሳያል" ።

ከቃል ኪዳኑ ጋር አብረን ልንመለከተው የሚገባን ሌላው ተምሳሌነት የስርየት መክደኛውን በተመለከተ ነው ። ይህ የታቦት መክደኛ ሲሆን የሚሠራውም ከንጹሕ ወርቅ ነበር ። ወርቅ የመለኮት ምሳሌ ሲሆን ምሕረት የሚገኘው ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ እንደሆነና እንደዚሁም በሰው ሥራ ሳይሆን በመለኮት ሥራ እንደሆነ ያመለክታል ። ለሰው ልጅ የኃጢአት ሥርየት የተገኘው መለኮት በሆነው በክርስቶስ እንደሆነ እንመለከታለን ።

ኦሪተ ዘጸአት ምዕራፍ 25 ቁጥር 17- 22 ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ትዕዛዝ ስንመለከት "የስርየት መክደኛውንም በታቦቱ ላይ ታደርገዋለህ እኔም የምሰጥህን ምስክር በታቦቱ ውስጥ ታኖረዋለህ ። በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ የእስራኤልንም ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል በስርየት መክደኛው ላይ ሆኜ አነጋግርሃለሁ " የሚል ክፍል እናገኛለን ። በዚህም መሠረት የስርየት መክደኛው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝበት ሥፍራ እንደሆነ

# መደምደሚያ

እንግዲህ የቃል ኪዳኑን ታቦት በተመለከተ የተለያዩ ሐሳቦችን አይተናል። ግራ የሚያጋቡና ብዙ ጥያቄዎችን ሊያስነሱ የሚችሉትን ሐሳቦች በመመርመር ወደ ትክክለኛው ሁኔታ ለመድረስ ሙከራ ተደርጓል ። ከዚህ ጽሑፍ በኋላ ሰፋ ያለ ውይይት በዚሁ ርእስ ላይ እንደሚነሳ ይገመታል ።

ኢትዮጵያና የቃል ኪዳኑን ታቦት በተመለከተ ከአመጣጡ ይልቅ ሥርዓቱ ከአይሁድ እምነት ወደ ክርስትና ይዘት መሸጋገሩ የበለጠ የተወሳሰበ ሆኖ እናገኘዋለን ። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በአመጣጡ ላይ እስከአሁን ያሉት ሐሳቦች ሁለት ናቸው ።

- እንደ ክብረ ነገሥት ዘገባ እና
- እንደ እንግሊዛዊው ጸሐፊ ግራሃም ሀንኮክ አገላለጽ ናቸው።

ሦስተኛው ሐሳብ እንዲያውም ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣ አይችልም የሚለው ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ የሙሴ ወይም የአይሁዳውያን የታቦት ሥርዓት እንዴት ክርስትና ይዘት ሊሰጠው እንደቻለ በየትኛው ዓመተ ምህረት፥ በየትኛው መንግሥት በእንዴት ያለ ትዕዛዝ ፥ እንደገናም በቤተ ክርስቲያን ትዕዛዝ እንደሆነና እንዳልሆነ የሚያመለክት አንዳችም የጽሑፍ ማስረጃ ማግኘት አይቻልም ። በመሆኑም በጽሑፉ ፍፃሜ መዳረሻ ላይ በሚከተሉት አብይ ጉዳዮች ላይ ማተኮር አስፈላጊ ይሆናል ።

1) ታቦቱ የት ነው ያለው?

በመጀመሪያ ደረጃ የቃል ኪዳኑ ታቦት ከእሥራኤል ከአይሁዳውያን ዘንድ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደመጣ የሚመለከተው ሐሳብ ነው። በጽሑፉ እንደተመለከትነው በኢትዮጵያውያኖች ዘንድ የሚታመንበትና ክብረ ነገሥት የሚገልጸው አመጣጥ በንጉሥ ሰለሞን ዘመነ መንግሥት ንግሥት ሳባ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛ ከንጉሡ አርግዛ የወለደችውና ምኒሊክ የተሰኘው ልጇ ከእሥራኤል የኢትዮጵያ ንጉሥ ለመሆን ተቀብቶ ሲመለስ ከእርሱ ጋር እንዲሄዱ የተመረጡት

እሥራኤላውያን ካህናት ከቤተ መቅደሱ ውስጥ ሠርቀውት እንዳመጡት የሚገልጸው የመጀመሪያው ሐሳብ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በተለይም በግራሃም ሀንኮክ በተጻፈውና The Sign and the Seal በተሰኘው መጽሐፍ እንደተጠቀሰው ከንጉሥ ሰለሞን ዘመነ መንግሥት እጅግ ቆይቶ በንጉሥ ምናሴ ዘመነ መንግሥት ታቦቱ ከኢየሩሳሌም ወደ ግብጽ መጥቶ በዚያም ለረጅም ጊዜ ከቆየ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ የሚያመለክተው ነው:: ለመጀመሪያው ሐሳብ ከክብረ ነገሥት በስተቀረ ጠንካራ የሆነ ሌላ ደጋፊ ማስረጃ አልተገኘም :: ከዚህ በተጨማሪም ንግሥት ሳባ እራሷ ኢትዮጵያዊት ለመሆኗ የሚጠራጠሩ ሊቃውንትና ተመራማሪዎች አሉ :: በተለይም ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ምርምርና ጥናት የሚደረግበት የየመን ተወላጅ ናት የሚል አመለካከት አለ ይህንን ሐሳብ ከአረቢያ ታሪክና ከእስልምና ሃይማኖት ጽሑፎች ጋር በማገናዘብ ለመመልከት ሞክረናል ::

ከፍ ሲል የተጠቀሱት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሐሳቦች በንጉሥ ሰለሞን ዘመን ይሁን አልፎም በንጉሥ ምናሴ ዘመን የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣቱ ይስማማሉ :: ሆኖም የክብረ ነገሥት ዘገባ ደጋፊ ማስረጃ ስለሌለው ግራሃም ሀንኮክ ያቀረቡትን ዘገባ ለመቀበል ይቀላል :: የእርሳቸው ዘገባ በሚከተሉት መረጃዎች ይደገፋሉ ::

ሀ. በግብጽ ተሠርቶ የነበረው የአይሁዶች ቤተ መቅደስ ዋነኛው ማስረጃ ነው ::
ለ. ታቦቱ በጣና ሐይቅ ደሴቶች እንደነበረ በተመለከተ ከመምህር ፍስሐ የተገኘው አፈ ታሪክ ::
ሐ. የእሥራኤላውያን ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥ አስመልክቶ ከካህን አዳነ የተገኘው መረጃ ::
መ. በጣና ቂርቆስ የተገኘው ከድንጋይ የተጠረበው የደም መስዋዕት ማጠራቀሚያ ::
ሠ. በዝዋይ የሚገኘው ታሪክና የሕዝቡ ቋንቋ ናቸው ::

በሌላ በኩል የታቦቱን ወቅታዊ ሥፍራ አስመልክቶ ካናዳዊው ግራንት ጀፍሪ ያቀረቡት መረጃ ማለትም በድብቅ ወደ እሥራኤል ተወስዷል የሚለውን ለመቀበል በጣም አስቸጋሪ ይሆናል ::

በተመሳሳይ ሁኔታም አስትራሊያዊው አርኪኦሎጂስት ጆናታን ግሬይ ያጠናቀሩት ግኝት ምንም እንኳ መንፈሳዊውይዘቱ የሚማርክና

የሚመስጥ ቢሆንም በኢየሩሳሌም ከተማ ቀራንዮ ወይንም ጎለጎታ ተብሎ በሚጠራው ሥፍራ ይገኛል ብሎ ለማለት ያዳግታል ።

በዚሁ አንፃር ደግሞ በጽሑፉ እንደተመለከትነው በአይሁዶች ዘንድ የተለያዩ እምነቶች ይገኛሉ ። ከነዚህም መካከል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ዋነኛው አመለካከት የቃል ኪዳኑ ታቦት በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በነቢዩ ኤርሚያስ ተደብቋል የሚለው ይሆናል ። ለዚህም ማስረጃ የሚቀርበው የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት በሚቀበሉት በሰማንያ አሃዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፤ በመጽሐፈ መቃብያን ተጽፎ መገኘቱ በጣም የሚያሳስብ ነው ። ከዚህም በላይ በአማሪኛ ትርጉም ላይ የሚገኘው ጽሑፍና ሌላው የመቃብያን መጽሐፍት ልዩነት ማሳየታቸው የተለየ ነጥብ የሚጥል ሆኖ እናገኘዋለን ። ለምን ይህ ክፍል ከሌሎች ሊለይ ቻለ ? ድንገትም ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር በተያያዘ ይሆን? ከክብረ ነገሥት ዘገባ ጋር የሚለይ ስለሆነ ግጭት ወይም ቅራኔ እንዳይፈጥር ትርጉሙ የተለየ ሆኖ ይሆን ?

## 2) ክርስትና ይዘቱ

በሁለተኛ ደረጃ ልንመለከተው የሚገባው የመደምደሚያ ሐሳብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የቃል ኪዳኑ ታቦት ከሙሴ/ከአይሁዳውያን ጋር በተያያዘ የተሰጠው የክርስትና ይዘት እና ትርጉም ይሆናል።

እንደምናውቀውና በጽሑፉ በሰፊው ለመመልከት እንደሞከርነው ፥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከብሉይ ኪዳንና ከአይሁዳውያን ሥርዓት በተያያዘ የሚከናወነው ሥርዓት ታቦት የተለየ ነው ። በአቡነ ጎርጎርዮስ አገላለጽም ሆነ በሌሎች የቤተ ክርስቲያኒቱ አቋም (መሠረተ እምነት) ጸሐፊዎች መሠረት የብሉይ ኪዳን ሕግጋት እየተረጎመች በክርስትና ይዘት በሥራ ላይ ያዋለች ኢትዮጵያ ብቻ ናት ። ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ወይም የቃል ኪዳኑ ታቦት ሥርዓት ምስጢር አልገባቸውም ወይም ንቀውት አይጠቀሙበትም።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የታቦቱ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ነው ። ያለ ታቦቱ ቤተ ክርስቲያን ሊኖር አይችልም፥ ቤተ ክርስቲያን ያለ ታቦት ባዶ ሕንፃ ትሆናለች ። የቃል ኪዳኑም ታቦት የሚያገለግለው የጌታን የሥጋ ወደሙ ፥ የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት መፈተቻ/ማስፈጸሚያ ነው።

በዚህ ሐሳብ ላይ ከሁሉ በፊት ሊነሳ የሚገባው ነጥብ በታቦትና በጽላት መካከል ያለው ተመሳሳይነት እና ልዩነት ነው ። በአገራችን በተለይም በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ እነዚህ ሁለት ቃላት በማለዋወጥ ያለ ምንም ልዩነት በጥቅም ላይ ይውላሉ ። ሁለቱም ግን በጣም የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው ።

ብዙ ጊዜ ይህ ችግር የሚታየው ቀለል ባለ ትኩረት ነው ። ሆኖም ግን አሳሳቢነቱ ከፍ ያለ ነው ። ይህንንም ምክንያት የኢትዮጵያን የታቦት ሥርዓት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኘው የታቦት ሥርዓት ጋር በምናነጻጽርበት ጊዜ ግልጽ ሆኖ እናገኘዋለን ። ይህንን ሃሳብ በጽሑፉ በሦስተኛው ምዕራፍ ላይ ተመሳሳይነቱንና ልዩነቱን በተመለከትን ጊዜ ዳስሰነዋል ። ዛሬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኘው "ታቦት" ተብሎ የሚጠራው ፣ ጽላት ማለትም ሠሌዳው ብቻ ሲሆን እንደ አይሁዳውያን ሥርዓትና እንደ እግዚአብሔር ትዕዛዝ ፥ እንደ ሙሴም አሠራር ታቦት ማለት የጽላት(ቶች) ማስቀመጫ በወርቅ የተለበጠ አራት ማዕዘን መሰል ሳጥን/ማደሪያ ታቦት የለም ። በመጀመሪያ ደረጃ በየአብያተ ክርስቲያኑ እንደ አሪት ዘጸአት ትዕዛዝ መሠረት ታቦት ለመሥራት እጅግ በጣም ብዙ ውጪ የሚጠይቅ ይሆናል ። ስለሆነም የማይቻል ነገር ነው ። በየአብያተ ክርስቲያኑ የሚገኘው ታቦት/ማደሪያው ሳይሆን ጽላተ ሠሌዳው ብቻ ነው ። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ለሙሴ በጣቱ አሥርቱን ትዕዛዝት ጽፎ የሰጠውን ሁለቱን ጽላቶች የሚመስል ማለት ነው ።

በጽሑፉ እንደተመለከትነው አባ ኪዳነ ማሪያም ጌታሁን ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ በሚለው ጽሑፋቸው ከሁለቱ አንዱ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ያሉት ይህንኑ ይሆናል !

ለዚህ ተጨማሪ ማስረጃ ቢያስፈልግ አቡነ ጎርጎርዮስ ፥ ብርሃኑ ጎበና እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይ የሆኑ መሪ ጌታ የገለጹትን መጥቀስ ይቻላል ። ይኸውም አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚመሠረትበት ጊዜ ከእጽ ወይም ከእምነበረድ ተቀርጾ የእግዚአብሔር ሚስጥራዊ ስም (ኅቡዕ ሥም) አልፋና አሜጋ ይፃፍበታል ። ይህ ከተጻፈበት በኋላ በኤጲስ ቆጶስ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ በመንበሩ ይሰየማል ። ይህም ጽላቱ መሆኑ ነው ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ሲመሠረት የሚቀረጸው ጽላተ ሰሌዳው እንጂ ታቦቱ አይደለም ።

ሌላው ጥያቄ የሚፈጥረው ደግሞ ከአንድ በላይ ቅጂ ታቦት መኖሩ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ውጪ መውጣት አይሆንም ወይ ?

የሚል ነው ። እሥራኤላውያን ያንን ያህል ዘመን ሲኖሩ ለምን ሌላ ቅጂ አልሠሩም ? በተለይም ተሰደው በተለያየ ሥፍራ ሲኖሩ ተበትነው በያሉበት ለማምለኪያ እንዲሆናቸው ፤ እንደገናም ታቦቱ በፍልስጤማውያን ተማርኮ ተወስዶባቸው በነበረ ጊዜ ያለ አምልኮ አንቀርም በማለት ለምን ሌላ የኪዳን ታቦት አልሠሩም ? አለበለዚያም ታቦቱ በቀደማዊ ምንሊክ እጅ ከተወሰደ በኋላ መተኪያ ሌላ ለምንለ አልሠሩም? ይህ ብቻ አይደለም ፤ በጽላቱ ላይ የሚጻፈውስ ቃል ለምን ተቀየረ ? በብሉይ ኪዳን የነበረው አሥርቱ ትዕዛዝ ለምን አሁን በእግዚአብሔር ሥም ተተካ ?

ከዚህ በተረፈ እነዚህን ልዩነቶች በተመለከትን ጊዜ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አቋም መሠረት ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና የአይሁድ እምነት ተከታይ ስለነበረች ክርስትና ወደ አገሪቱ በገባ ጊዜ ከአይሁድ ባህል የሚጠቅማትን ይዛ እንደቀጠለች ተመልክተናል ። ከነዚህም መካከል የአይሁድ ሰንበት (ቅዳሜ) ፥ መገረዝ ፥ የርኩስና የቅዱስ ምግብ ደንብ እና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል ። ሆኖም ግን ይህንን ጉዳይ በጂአግራፊ አቀማመጧ ቅርበት ካላት ከግብጽ የአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ባነጻጸርን ጊዜ ልዩነት እንደተከሰተ ተመልክተናል ። በአዲስ ኪዳን ቅዱስና ርኩስ ምግብ እንደሌለ የግብጽ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ ገልጸዋል ።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽም " የጌታ ኢየሱስ ተከታይ እንደመሆኔ መጠን ርኩስ የሆነ ምግብ እንደሌለ በእርግጥ አውቃለሁ " ይላል (ሮሜ ም 14 ላይ) ። በተጨማሪም የታቦት ሥርዓቱን በተመለከተ ይህ በሐዋርያት ማለትም በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የተደነገገ እና ከእነርሱ በኋላ በተውፊት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሥርዓት እንዳልሆነም ተመልክተናል ። በተለይም የታቦት ሥርዓት ከቅዱስ ቁርባኑ ጋር በተያያዘ በእነርሱ ዘንድ እንዳልነበር ግልጽ ነው ።

ይህንንም ሰፋ አድርገን የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓተ ክንውን በመጽሐፍ ቅዱስ አስረጅነትና በታሪክ ማህደር ደጋፊነት የተመለከትነው ጠለቅ ያለ አመክሮና ጥናት የሚጠይቅ ይሆናል ። ከዚህ በተጨማሪ የአይሁድ ባህልና ሥርዓት መጠበቅ በሚመለከት ካለይ የተመለከትናቸው ጉዳዮች በሙሉ ከአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመተዳደሪያ ደንብ ማለትም ከፍትሐ ነገሥት ጋር ባመሳከርንበት ጊዜ ትልቅ ውዝግብ ፈጥሯል ። ይህ የቤተ ክርስቲያን የመተዳደሪያ ደንብ ከግብጽ ኢብን አሳሳል በተሰኘ ግብጻዊ በአረቢኛ

ተጽፎ ፥ ከአበሪኛም ወደ ግዕዝና ወደ አማሪኛ ተተርጉሞ በቤተ ክርስቲያኒቱ በሥራ ላይ የዋለ ሰነድ ነው ። በዚሁ መዝገብ ዛሬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሚጠበቁት ሥርዓቶች ጋር ከፍተኛ ቅራኔ ያሳያል ። ለምን ? እንዴትስ እስካሁን ሳይተችበትና ሳይታረም ቀረ ? ሌላ መልስ የሚሻ ጥያቄ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚካሄደው ሥርዓተ ታቦት ከአይሁዳውያን ወይም በብሉይ ኪዳን ካለው ሥርዓተ ታቦት ጋር ያለው ልዩነት እንደዚህም በአጠቃላይ የአይሁድ ባህሎችንና ሥርዓቶችን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ ያለው ሁኔታ ይህንን ሲመስል በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ታቦት/ሥርዓተ "ጽላት" ከብሉይ ኪዳኑ/ከአይሁዳውያን ሥርዓት ይልቅ ቅርበትና ተመሳሳይነት የሚያሳየው በተለይም ከግብጽ እንደዚሁም ከሶርያ ፥ ከአርመንና ሌሎች የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሥርዓት ጽላት ጋር ነው ። ይኸውም በግብጾች ዘንድ "ሉሕ" ተብሎ ከሚጠራው ጋለት ነው ። ይኼ መመሳሰል ደግሞ በጽሑፉ መጀመሪያ ላይ ይዘነው ለተነሳነው ጥያቄ መመለሻ ቁልፍ ይሆናል ።

1ኛ)- በሁለቱም ሥርዓቶች ጥቅም ላይ የሚውሉት ጽላቶች/ ሠሌዳዎች ናቸው ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ ጽላቱ ከእንጨት ወይም ከጽላት ይቀረጻል ። በግብጾች ዘንድ ጽላቱ ከእንጨት ይሠራል ። (በአይሁዳውያን ዘንድ የነበሩት ሁለት ጽላቶች ከድንጋይ የተቀረጹ ነበሩ) ።

2ኛ)- በሁለቱም ሥርዓቶች ውስጥ ጽላቶቹ በመሠውያው ላይ ይቀመጣሉ ። (በአይሁዳውያን/በብሉይ ኪዳን ሥርዓት ጽላቶቹ በታቦቱ/በማደሪያው ይቀመጥ ነበር) ።

3ኛ)- በሁለቱም ሥርዓቶች የሚኖረው ወይም የሚያስፈልገው ጽላት አንድ ብቻ ነው ። (በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አሠራር መንበሩ ከአንድ በላይ በሚሆን ቅዱሳን ወይም መላእክት ሊሰየም ስለሚችል ደባል ጽላት ሊኖር ይችላል ። በብሉይ ኪዳን ሥርዓት ሁለት ጽላቶች ነበሩ) ።

4ኛ)- በኢትዮጵያና በግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚጻፈው ጽሑፍ "አልፋና ኦሜጋ" የሚለው የእግዚአብሔር ሥም ተመሳሳይነት ያሳያል ። (በብሉይ ኪዳን በነበረው ጽላቶች ላይ የተጻፉት አሥርቱ ትዕዛዛት ነበሩ) ።

5ኛ)- በሁለቱም በኢትዮጵያም ሆነ በግብጽም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የጽላቶች አገልግሎት ከቅዳሴ እና ከቅዱስ ቁርባን ሥርዓት

ጋር የተያያዘ ነው ።

እነዚህ ካለይ የተመለከቱት ነጥቦች እንደሚያመለክቱት በኢትዮጵያ የሚገኘው ሥርዓተ ታቦት ቅርበቱ ከብሉይ ኪዳን ፥ ከአይሁዳውያን ሥርዓት ይልቅ ከግብጻውያን ሥርዓት ጋር እንደሆነ ግልጽ ነው ። እንደሚታወቀው ሁሉ ከንጉሥ ኤዛና ዘመነ መንግሥት አንስቶ በአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ተጀምሮ እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት ድረስ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ይሾሙ የነበሩት ከግብጽ ነበር ። መሠረተ ትምህርቱ ፥ ቀኖናውና የቤተ ክርስቲያኒቱ የመተዳደሪያ ደንብ ጨምሮ የተገኘው ከግብጽ ነው ። ፍትሐ ነገሥት ከአረቢኛ ወደ ግዕዝ ከዚያም ወደ አማሪኛ የተተረጎመ እንደሆነ ቀደም ብለን ተመልክተናል ።

እንግዲህ እስከአሁን የተመለከትናቸውን ሐሳቦች በአጠቃላይ ከግንዛቤ በማስገባት ልንደረስበት የምንችለው መደምደሚያ በሁለት ዓይነት መንገድ ሊገለጽ ይቻላል ።

በመጀመሪያ ደረጃ በብሉይ ኪዳን በሙሴ አማካኝነት በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የተቀረጸው የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ኢትዮጵያ አልመጣም ፤ ሊመጣ አይችልም ፤ ታቦቱ

ሀ. እንደ አይሁዳውያን ታሪክ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሰለሞን ሠርቶት በነበረው ዋሻ ውስጥ ተደብቋል ፥ ወይም

ለ. እንደ መጽሐፍ መቃብያን አገላለጽ በነቢዩ ኤርሚያስ አማካኝነት በተራራ ላይ ተደብቋል ፥ እግዚአብሔር ወደ ፊት ሥፍራውን ይገልጸዋል ፥ ወይም ደግሞ

ሐ. በባቢሎናውያን ተማርኮ አቅልጠው ተጠቅመውበታል ፥

መ. ታቦቱ የሚገኘው በቀራንዮ/በጎለጎታ ጋር ሥር ነው የሚሉትን ሐሳቦች በሚደግፉት በኩል ተቀባይነት የሚያገኘው መደምደሚያ ሲሆን ፥ ይኸውም በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚደረገው የታቦት/ጽላት ሥርዓት በብሉይ ኪዳን ከሚገኘው የቃል ኪዳን ታቦት ጋር በይዘትም ሆነ በሥርዓት ደረጃ በፍጹም ተመሳሳይነት ስለሌው ይህ የተወረሰው ከግብጻውያንና ከሌሎች ምሥራቃዊ አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከሚገኘው ሥርዓተ ጽላት (ሉሕ) ነው ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ በክብረ ነገሥት አማካኝነት የሚታወቀው አፈ ታሪክ ስለነበረ እነዚህን ሁለቱ በአንድ ላይ ተቀናኝተው አሁን በአብያተ ክርስቲያኒቱ የሚገኘው ሥርዓት አቋም ሊመሠረት ቻለ የሚል ይሆናል ።

በሁለተኛ ደረጃ የምንደርስበት ሐሳብ በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰው የቃል ኪዳኑ ታቦት በኢትዮጵያ ይገኛል በሚለው አቋም

ላይ የተመሠረተ ሲሆን ፤ ታቦቱ የመጣው እንደ ክብረ ነገሥት ዘገባ በንጉሥ ሰለሞን እና በንግሥት ሳባ ዘመነ መንግሥት ፥ በልጆቻቸው በቀዳማዊ ምኒሊክ አማካኝነት ነው የሚለውም ሆነ እንደ እንግሊዛዊው ግራሃም ሀንኮክ አገላለጽ ታቦቱ የመጣው ምናሴ ዘመን መንግሥት በግብጽ አድርጎነው የሚለው ሐሳብ ቢሆን ልዩነት አያመጣም ፡፡

ነገር ግን ታቦቱ በኢትዮጵያ በመገኘቱና በንጉሥ ኤዛና ዘመነ መንግሥት በፍሬሚናጦስ አማካኝነት ክርስትና በአገሪቱ ሲመሠረት ከዚያም በኃላም ፍሬሚናጦስ በግብጽ ፓትርያሪክ አማካኝነት አባ ሰላማ ተብለው የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ ሆነው ሲሾሙ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ይዘው በመጡት መሠረት ሥርዓተ ጽላትን (ሉሕ) በኢትዮጵያ ሲመሠረቱ፥ ኢትዮጵያ የታቦቱ ባለቤት ስለነበረች ከጊዜ በኃላ ከክብረ ነገሥት ጋር እና በአገሪቱ ከሚገኘው ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ይህ የጽላት ሥርዓት (ሉሕ) ተያያዘ የሚል ሐሳብ ይሆናል ፡፡

በአጭሩ የመጀመሪያው መደምደሚያ የኪዳኑ ታቦት በኢትዮጵያ ባይኖርም ታሪኩ በክብረ ነገሥት አማካኝነት ስለነበረ ከግብጽ የመጣው ሉሕ ሥርዓት ከዚህ ታሪክ ጋር ተያያዘ የሚል ሲሆን ፥ በሁለተኛ ደረጃ የተመለከተነው መደምደሚያ ደግሞ ታሪኩ ብቻ ሳይሆን ታቦቱ በአካል በአገሪቱ ውስጥ ይገኝ ስለነበረ የግብጻውያኑ ሥርዓት ከዚህ ጋር ተያያዘ የሚል ነው ፡፡

ይህ ብዙ ሊያነጋግር የሚችል ቢሆንም በእርግጠኛነት ልንናገር የምንችለው ግን በኢትዮጵያ የሚገኘው የታቦቱ ሥርዓት የክርስትና ይዘት የሚያተኩረው በቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ፍጻሜ ላይ እንደመሆኑ መጠን ከዚህ ጋር በተያያዘ ክርስትና ከተወለደበት ከኢየሩሳሌም ከተማ እንደዚሁም ከክርስቶስ እርገት በኋላ ከሐዋርያት ዘመን ሥርዓት ጋር በፍጹም ግንኙነት የሌለወንና ፤ እንደገናም የሐዋርያት ተውፊት የተከተለ እንዳልሆነ ነው ፡፡ ቀደም ሲል በጠቀስናቸው ገለፃዎች መሠረት ኢትዮጵያ (ማለትም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን) የአይሁዳውያንን ሥርዓት ወደ ክርስትና ይዘት እየተረጎመች ተጠቀመችበት እንጂ በሐዋርያት ዘንድ ይከናወን የነበረ ሥርዓት እንዳልሆነ እርግጥ ነው ፡፡

በግብጻውያን ዘንድ ባለው ተውፊት መሠረት በየቦታው እየተዘዋወሩ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትን ይፈጽሙ የነበሩ ካህናት ሥርዓተ ቁርባን ለመፈጸም በተውፊታቸው መሠረት በድንጋይ መሠውያ መጠቀም ስለማይችሉ "ሉሕ" ወይም ከእንጨት የተሠራ ጽላተ ሠሌዳ ይዘው ይዘዋወሩ እንደነበረ ከአባ አንቶኒዮስ ባገኘነው

መረጃ ተመልክተናል። ነገር ግን ይህ ሥርዓትና ተውፊት በብሉይ ኪዳን ከሚገኘው ከቃል ኪዳን ታቦት/ወይም ጽላት ጋር አንዳችም ግንኙነት የለውም ። ሆኖም ግን ይህ ሥርዓት ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በአገሪቱ ከሚገኘው የቃል ኪዳኑ ታቦት (ወይም ደግሞ ታሪክ) ጋር ተያያዞ አሁን የምንመለከተውን አስገኝቷል ማለት ነው ።

በሐዋርያት የነበረውን የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓት ስንመለከት በመጀመሪያዎቹ ሁለት መቶ ዓመታት ገደማ ድረስ ሥርዓቱ በገበታ ዙሪያ ይደረግ የነበረ ሲሆን በዚህም እንደ ግብጻውያኑም ሆነ እንደ ኢትዮጵያ ሥርዓት ጽላት ወይም ሉሕ አልነበረም ። ሥርዓቱ በግብዣ መልክ ፥ ምዕመኑ ምግብ አዘጋጅተውና መጠጥ ይዘው በሚሰበሰቡበት ሥፍራ እየወሰዱ በዚያም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ መቆረስና ደም መፍሰስ እያሰቡ የሚያደርጉት የአንድነት ጊዜ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከታሪክ ማህደር ተገናዝቦ ቀደም ሲል ተመልክቷል ።

የታቦቱ ክርስትና ይዘት በተመለከተ የምንደርስበት መደምደሚያ ይህ ሲሆን ወደፊት ከክርስቶስ ምጽአት ጋር በተያያዘ ደግሞ ያለውን አመለካከት ስንገመግም ምንም እንኳ በአክሱም ይገኝ የነበረው የቃል ኪዳን ታቦት በእሥራኤለውያን አማካኝነት በሥውር ተወስዷል አሁንም በእሥራኤል ይገኛል የሚለውን እና የለም ታቦቱ ከመጀመሪያው አንስቶ እዚያው በኢየሩሳሌም ከተማ ዋሻ ውስጥ ነበር የሚለውን ዘገባ ለመቀበል የሚያስቸግር ቢሆንም ፥ ለሦስተኛና ለመጨረሻ ጊዜ የአይሁዶች ቤተ መቅደስ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መሠረት የሚታደስ እና ታቦቱ በዚህ ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚቀመጥ ለመሆኑ ጥርጥር አይኖረውም ። ዋነኛ ፥ ማዕከል ያለው የአምልኮቱ ዕቃ እንደመሆኑ መጠን ማለት ነው ። ስለሆነም ይህንን ጊዜ በናፍቆት እና በጉጉት የሚጠበቅ ይሆናል ።

ከዚህ በተረፈ ለየት ባለ ሁኔታ ለመድረስ የምንችልበት ሌላ አማራጭ አለ ። ይኸውም እንደ አባ ኪዳነ ማሪያም ጌታሁን እና እንደ ፈረንሳዊው J Coulbeaux (Histoire Poltique et Religieuse de l'Abyssinie) አገላለጽ ድንገትስ ጽላትና ታቦት በሚሉት ሁለት ቃላት መካከል ልዩነት የሌለ እንደሆነስ ! ድንገትስ ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ተሰርቆ የመጣው እንዳለ ታቦቱ ሳይሆን ከሁለቱ አንዱ ጽላት ብቻ እንደሆነስ !

በመጀመሪያ ደረጃ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው ሥርዓት ማለተም ታቦት ተብሎ የሚጠራው ጽላቱ መሆኑ እንደገናም በካህናት ራስ መሸከም ያስፈለገበት ምክንያት

በመጨረሻም ከእሥራኤላውያን ጋር ልዩነት (ምዕራፍ3) ማሰየቱ መልስ አገኘ ማለት ነው ::

በሁለተኛ ደረጃ ዋናው ታቦት ፥ የጽላቱ ማደሪያ ፤ በውስጡ አንደኛውን ጽላት ብቻ ይዞ ወዴት ሄደ ይባላል ? በጽሑፉ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በነቢዩ ኤርሚያስ በተራራው ላይ ተደብቋል ማለት ነው ? ወይስ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ ንጉሥ ሰለሞን ባዘጋጀው ድብቅ ዋሻ ውስጥ ይሆን ያለው ?

አለበለዚያስ አስትራሊያዊው አርኬኦሎጂስት በዋሻ ውስጥ ያገኙት ሳጥን መሰል ዕቃ በእርግጥ ታቦቱ ከሆነ በውስጡ ያለው አንድ ጽላት ብቻ ነው ? እንደዚህ ካልን ደግሞ ካናዳዊው ጸሐፊ ግራንት ጀፍሪ በድብቅ በእሥራኤላውያን ከኢትዮጵያ የተወሰደው ምንድን ነው ? ጽላቱ ወይስ ታቦቱ ?

በሌላ አንጻር ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ደንብ መሠረት በጽላቱ ላይ የሚጻፈው የእግዚአብሔር ስም ተሰርቆ ከመጣው ጽላት ላይ የተወረሰ ሳይሆን ከግብፃውያን "ሉሕ" ላይ የተወረሰ ነው ማለት ነው !

ሌላ ሊያስኬድ የሚችል አማራጭ !!!!!!

# ለጽሑፉ ድጋፍ የሆኑ መጽሐፍት

# (References)


1) መረሐ ጽድቅ ባህለ ሀይማኖት - በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን - ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የታተመ - አ.አ 1988 ዓም
2) ዓምደ ሀይማኖት - ብርሃኑ ጎበና - አዲስ አበባ 1985 ዓም
3) ፍኖተ ጽድቅ - ብርሃኑ ጎበና - አዲስ አበባ 1986 ዓም
4) ኆኅተ ሃይማኖት - ብርሃኑ ጎበና - አዲስ አበባ 1987 ዓም
5) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ - አባ ጎርጎሪዮስ (ሊቀ ጳጳስ) አአ 1974 ዓም
6) ኢትዮጲስ - ግርማ ዘውዴ
7) ትምህርተ መለኮት - ዓሥራት ገብረ ማሪያም አአ 1983 ዓም
8) ክርስቶስ በማደሪያው ድንኳን - ዶ/ር ዓለሙ ቢፍቱ
9) ፍትሐ ነገሥት - የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
10) ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ (ከመሻሻል ጋር) - አባ ኪዳነ ማሪያም ጌታሁን 1957 ዓም
11) መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት) የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር - እአአ 1962
12) Miguel F Brook - Kebra Negest, Red Sea Press Inc, 1996
13) Sir E A Wallis Budge - Ethiopia and the Ethiopians -
14) Sir E A Wallis Budge - Queen Sheba and her only Son Menelik
15) Butler - Ancient Coptic Churches of Egypt
16) J Coulbeaux - Histoire politique et religieuse de l'Abbyssinie
17) Signs of the Gods? Erich Von Daniken (translated by Michael Herm)
18) Archdeacon Dowling - The Abyssinian Church

19) Montague Fowler - Christian Egypt

20) Belai Giday - Ethiopian Civilisation, Addis Ababa, 1992

21) Graham Hankock - The Sign and the Seal, London 1992

22) M.H Hyatt - Church of Abyssinia

22) Grant Jeffrey - Armageddon Appointment with Destiny, 1988

23) Grant Jeffrey - The Ark and the Red heifer (Video)

24) David Kessler - The Falashas , Great Britain, 1982

25) David Levi - The Tabernacle, Shadows of the Messiah

26) Rev A F Matthew - The Teaching of the Abyssinian Church

27) Richard Pankhurst - Social History of Ethiopia

28) K S Pedersen - Les Ethiopiens fils d'Abraham

29) Tadesse Tamerat - Church and State in Ethiopia, Oxford 1972

30) Edward Ullendorf - Ethiopia and the Bible

31) E.S Drower - Water into Wine, 1956 London

32) Matthew Henry's Commentary

33) Encyclopedia Judaica.